# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 339 ነሐሴ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!
















# በመዲናዋ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶች የነገዋን የአዲስ አበባ መልክ የሚቀይሩ ናቸው

- የ'አዲስ ቱሞሮ' የኢኮኖሚ ዞን ግንባታ ተጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በመዲናዋ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶች የነገዋን የአዲስ አበባ መልክ የሚቀይሩና ለኑሮ ምቹ የሚያደርጉ ናቸው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። የ'አዲስ ቱሞሮ' የኢኮኖሚ ዞን ግንባታ መጀመሩን ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንት በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ ከሥራ ውጭ ሕልማችንን የምንፈታበት ሌላ መንገድ ስለሌለ ያለን የፖለቲካ ዕሳቤ ሥራ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የመዲናችንን የነገ መልክ የሚያሳየውን የ'አዲስ ቱሞሮ'

**በመዲናዋ የሚገነቡ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**

# የቴክኖሎጂ ፈጠራ ተምሳሌቶች

**ሄለን ወንድምነው**

**ዜና ሐተታ**

የዓለም ሀገራት የቴክኖሎጂ አቅምና አጠቃቀማቸው በእጅጉ ተለውጧል። ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂ ከሚያስገኛቸው በረከቶች ተጠቃሚ ለመሆን በዘርፉ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራት የግድ ይላታል፡፡

ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊዎችና ወጣቶች ክህሎታቸውን እያዳበሩ፣ ሀገራቸውን በቴክኖሎጂ ከበለፀጉ ሀገራት ተርታ እንዲያሰልፉ እና ከተረጅነትና ከተቀጣሪነት አስተሳሰብ ወጥተው ሥራ ፈጣሪ መሆን የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ከባለድርሻ

**የቴክኖሎጂ ፈጠራ.. ወደ ገጽ 6 ዞሯል**

# ጠንካራ ቁጥጥርንና የማምረት ትጋትን የሚጠይቀው ማሻሻያ

**ማርቆስ በላይ**

**ዜና ትንታኔ**



በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሰበብ ምርት በመሰወርና ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ በሕገወጥ ተግባር ላይ በተሰማሩ ነጋዴዎች ላይ ሕጋዊ ርምጃ እየተወሰደ ነው። ሆኖም ማሻሻያው የሚያደርሰውን ጫና ለማቃለል ተጠያቂነትን ከሚያሰፍኑ ሥራዎች ያለፉ ተግባራት ያስፈልጋሉ፡፡

ለመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የሚመጡ ጫናዎችን ለመቅረፍ ሕጋዊ ርምጃዎችን ከመውሰድ ባለፈ ምን መደረግ አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ የዘርፉ ምሑራን ሀሳባቸውን ሰጥተውናል፡፡

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ተመራማሪ የሆኑት ሞላ ዓለማየሁ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፤ ምርት በሚደብቁ፣ በሚያሸሹ እና ዋጋ በሚጨምሩ ነጋዴዎች ላይ እየተወሰደ ያለው ሕጋዊ ርምጃና ሕግን

**ጠንካራ ቁጥጥርንና... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**






ቡልቶሳ ሂርኮ (ዶ/ር)

# ትምህርት ቢሮው ከ12 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2017 የትምህርት ዘመን ከ12 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ገለጸ።

የቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ቡልቶሳ ሂርኮ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ቢሮው ከሐምሌ ወር 2016 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤቶችን ምቹ የማድረግ፣ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን የመገንባት እና የማስዋብ ሥራ እንዲሁም መሠረተ ልማቶችን እንዲሟሉ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

በዚህም ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የትምህርት ቁሳቁሶች የመጠገን ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የገለጹት ቡልቶሳ (ዶ/ር)፤ በ2017 የትምህርት ዘመን ከ12 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በቀጣይ ሳምንት ከዞኖችና ከከተሞች ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ጋር የበይነ መረብ ውይይት እንደሚኖር ጠቁመዋል። በዚህም ከመማሪያ መጽሐፍ ስርጭት፣ ከትምህርት ቁሳቁስ እና ምቹ የትምህርት ከባቢን ከመፍጠር አንፃር የተከናወኑ የዝግጅት ሥራዎች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ይገመገማል ብለዋል።

እስከ አሁን ስድስት መቶ ሺህ የመማሪያ መጽሐፎች የተሰራጩ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህ ሳምንት ጀምሮ ደግሞ ተጨማሪ 600 ሺህ መጽሐፎች እንደሚሰራጩ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት ለመማሪያ መጽሐፍ ስርጭት በጀት የመደበ ቢሆንም የማተሚያ ድርጅቶች የሚጠበቀውን ያህል መጽሐፍ ማቅረብ አለመቻላቸውን ተናግረዋል።

በክልሉ አንድ መጽሐፉ ለሁለት ተማሪ በሚል እንኳን መጽሐፍ ለማዳረስ ቢሞከር 27 ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፎች እንደሚያስፈልግ የገለጹት ቡልቶሳ (ዶ/ር)፤ ቢሮው የተማሪዎች ምዝገባን በኦንላይን ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ጠቁመዋል።

በክልሉ የተማሪዎች ምዝገባ ከነሐሴ 27 እስከ ጷጉሜን 5 እንደሚካሄድ እና ተማሪዎቹ የሚመዘገቡበትን መንገድ የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህም በወረዳና በዞን የሚገኙ ባለሙያዎችን አሠልጥኖ ተማሪዎችን ለመቀበል በዝግጅት ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

በድርቅና በሌሎች ምክንያቶች ጉዳት ባጋጠማቸው አካባቢዎች ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶች እንዲያገኙ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር እየሠራን ያሉት ዶክተር ቡልቶሳ (ዶ/ር)፤ የትምህርት ቁሳቁስ የግዢ ሂደት እየተከናወነ መሆኑንም ነው የተናገሩት።

# የተጠገነው የእንስቶቹ ስብራት

**ዳግማዊት አበበ**

**ዜና ሐተታ**




ወጣት ምትኬ ገላና ወደ ማዕከሉ ከመቀላቀሏ በፊት አስከፊ ሕይወት ትመራ እንደነበር ትናገራለች፡፡ ቤተሰብ እንደሌላት የምትገልጸው ወጣቷ፤ በሰው ቤት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራች ትምህርቷን ስትከታተል መቆየቷንም ታስረዳለች፡፡

“ትምህርቴን ከምንም በላይ እወድ ነበር” የምትለው ወጣት ምትኬ፤ በኑሮ ጫና ምክንያት ግን ትምህርቴን ላቋርጥ ከጫፍ ደርሼ ነበር ትላለች፡፡

ትምህርቴን ላለማቋረጥና የኑሮ ጫናውን ለመቋቋም ትዳር ለመያዝ መወሰኗን የምትናገረው ወጣት ምትኬ፤ ሆኖም እንዳሰብኩት ሳይሆን ቀርቶ ኑሮ ከእጅ ወዳፍ ሆኖብኝ ነበር ስትል ያለፈውን ጊዜ ታስታውሳለች፡፡

ከወራት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሃሳብ አመንጪነት በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሴቶች ሥልጠና የሚያገኙበት የነገዋ ሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማዕከል ተመርቆ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ ከሰሞኑም ማዕከሉ በ18 የሙያ ዘርፍ ሲያሠለጥናቸው የቆየውን 302 ሠልጣኞች አስመርቋል። ከእነዚህ ሠልጣኞች መካከልም በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የነበረችው ወጣት ምትኬ አንዷ ናት፡፡

ወጣቷ ዕድሉን አግኝቼ ወደ ለነገዋ ማዕከል ስቀላቀል ከጠበኩት በላይ ሆኖ ነው ያገኘሁት የምትለው ምትኬ፤ እንደገባን የሕይወት ክህሎት ሥልጠናና የሥነልቦና ድጋፍ ተደርጎልን ወደ ሙያ ሥልጠናው እንድንገባ ተደርጓል ትላለች፡፡

ወጣት ምትኬ፤ በኤሌክትሪክና ቧንቧ ጥገና ሥራ መሠልጠኗን ገልጻ፤ ከሙያ ሥልጠናው ባለፈ ማኅበራዊ ትስስርን የሚጨምሩና የሥነ ልቦና የምክር አገልግሎት ሲሰጣቸው መቆየቱን ታነሳለች፡፡

ወደፊት በሠለጠንኩበት የሙያ ዘርፍ ወደ ሥራ ተሰማርቼ እራሴን በመለወጥ በእኔ ሕይወት እያለፉ የሚገኙ ወገኖችን መደገፍና ማስተማር እፈልጋለሁ የምትለው ምትኬ፤ እኔ ያገኘሁትን ዕድል ሌሎች ሴቶችም ዕድሉን ካገኙ ማሳለፍ እንደሌለባቸው ሃሳቧን ታካፍላለች።

ፍታሌ በቀለ ወደ ለነገዋ የሴቶች የተሐድሶና ክህሎት ማዕከል ሠልጥነው ከተመረቁ ሴቶች ውስጥ አንዷናት። ማዕከሉን ከመቀላቀሏ በፊት ተቀጥራ እንደምትሠራ ትናገራለች፡፡

ተቀጥራ በምሠራበት ተቋም ከሰዓት በላይ እንደሚያሠሯት የምትናገረው ፍታሌ፤ “ምግብ እንኳን ቁጭ ብዬ የምበላበት ጊዜ አልነበረኝም” ትላለች፡፡

ወደ ተቋሙ በሰዎች አማካኝነት እንደገባች የምትናገረው ወጣቷ፤ የመጀመሪያ ማዕከል ነው ሲባል ፍርሃት አድሮብኝ ነበር ስትል ያለፈውን ጊዜ ታስታውሳለች፡፡ ወደ ማዕከሉ ከተቀላቀልኩ በኋላ የነበረው ስሜት እንደፈራሁት አልነበረም የምትለው ወጣት ፍታሌ፤ ከምግብ አንስቶ እስከ መጠለያ ድረስ የነበረው አቀባበል ከሚባለው በላይ ሆኖ ነው ያገኘሁት ስትል ትናገራለች፡፡

ለአራት ወራት በግብርና ሙያ ላይ ሠልጥና እንደተመረቀች የምትናገረው ወጣቷ ሥልጠናውም ብቁ እንድንሆን አድርጎናል ትላለች፡፡

በሠለጠንኩበት የሙያ ዘርፍ ሠርቼ መለወጥን አስባለሁ የምትለው ፍታሌ፤ የከተማ አስተዳደሩም የመሥሪያ ቦታ ሼድ እንደሚሰጠንና በቅርቡ እንደሚያስረክበን ቃል ገብቶልናል ስትል ትገልጻለች፡፡

የአንድ ልጅ እናት የሆነችው ሜሮን አለሙ ወደዚህ ማዕከል ከመግባቷ በፊት በሴተኛ አዳሪነት ሕይወቷን ስትገፋ መቆየቷን ታስታውሳለች፡፡

ያሳለፈችውን ሥራ አስከፊነት የምትናገረው ወጣት ሜሮን፤ “ጨለማ ሕይወት ውስጥ ነበር የምኖረው” ትላለች፡፡ ወደ ማዕከሉ ስመጣ ነገ የተሻለ ይሆናል ብዬ ነበር ስትልም ታስታውሳለች፡፡

ከምንም በላይ በማዕከሉ ከተሰጠው ሥልጠና በላይ በተለይ እኔ ከነበርኩበት የሱስ ሕይወት እንድላቀቅና ወደ ራሴ እንድመለስ አድርጎኛል የምትለው ሜሮን፤ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ ስትል ትናገራለች ፡፡

በምርቃቱ ወቅት ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ በተግባር የተሰጠው ሥልጠና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተጨባጭ የሆኑ ውጤቶችን የሚያሳይ እንደሚሆን ይታመናል ።

የተመረቁት ሠልጣኞች ውስጣቸው አቅም እያለ አውጥቶ ለመጠቀም በሮች ስለተዘጉባቸው እንጂ ብቁዎች እንደሆኑ በአጭር ጊዜ ማሳየት ችለዋል ያሉት ከንቲባዋ፤ በዚህ ማዕከል ሠልጥኖ ብቁ መሆን ለበርካታ ሴቶች ስብራት መጠገን ምክንያት ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል።

የተመረቁ ሁሉም ሠልጣኞች የሥራ ዕድል እንደተመቻቸላቸው ጠቁመው፤ በቀጣይም ተመ ራቂዎች ማኅበራዊ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ማዕከሉ ኃላፊነት ሊወስድ ይገባል ብለዋል። ለሁሉም የመጀመሪያ ዙር ተመራቂዎች የሥራ ዕድል ማግኘታቸውን የጠቆሙት ከንቲባዋ፤ የከተማ አስተዳደሩ መሥሪያ ቦታ ማመቻቸቱን እና የተለያዩ ባለሀብቶች ደግሞ የመሥሪያ ዕቃዎችንና መነሻ ካፒታል ጭምር መደገፋቸውን ተናግረዋል።

ችግሩ በጣም ሰፊ በመሆኑ የበርካቶችን ትብብር እና አብሮ መሥራት ይጠይቃል ያሉት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ ለተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ወገኖችን ሕይወት ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፉም ጥሪ አቅርበዋል።

በሀገራችን በተለይም በመዲናዋ በተለያዩ ምክንያቶች ኑሯቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ በርካታ ዜጎች ይገኛሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ብዙውን ድርሻ ይይዛሉ ፡፡

በከተማዋ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስብራት የደረሰባቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመጠገን መንግሥት በርካታ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን ነድፎ እየሠራ ይገኛል፡፡

# ኮሚሽኑ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 37 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ከአደጋ ማዳን ችሏል

**መዓዛ ማሞ**



አዲስ አበባ፡ በ2016 በጀት ዓመት 37 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት ከአደጋ ማዳን መቻሉን የአዲስ አበባ እሳት አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ እሳት አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ 523 አደጋዎች ተመዝግበዋል።

ከዚህ ውስጥ 351 የሚሆኑት የእሳት አደጋዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ የጎርፍ፣ የኮንስትራክሽን እና መሰል አደጋዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ በደረሱት የእሳት አደጋዎች ምክንያት ሁለት ሰዎች ሕይወታቸውን ማጣታቸውንና የአደጋ ጊዜ ሠራተኞችን ጨምሮ 90 ሰዎች ላይ ቀላል እና ከባድ ጉዳት መድረሱን ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ በደረሱት አደጋዎች በንብረት ላይ አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የሚደርስ አደጋ መድረሱን ገልጸው፤ የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች ባደረጉት ርብርብ በአደጋ ውስጥ የነበሩ 156 ሰዎች ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ሕይወታቸውን መታደግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም ከ37 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ከአደጋ መታደግ መቻሉንም ገልጸዋል፡፡

በከተማ ውስጥ ከሚያጋጥሙ አደጋዎች የአብዛኛዎቹ ምክንያት የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን ገልጸው፤ ይህንን ለመከላከል ኮሚሽኑ በየክፍለ ከተማው ቤት ለቤት ጭምር ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች እንደሚሠራ ተናግረዋል፡፡ ለአደጋ ትኩረት በመስጠት ጥንቃቄ ከተደረገ አደጋዎችን ማስቀረትና የከፋ ጉዳት ሳያስከትል መከላከል እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

ኮሚሽኑ በየሳምንቱ መከላከል ላይ ያተኮሩ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንደሚያደርግ ተናግረው፤ በተጨማሪም በራሪ ወረቀቶች ለከተማዋ ነዋሪዎች እንዲደርስ ይደረጋል ብለዋል፡፡

አሁን ላይ ከተማዋ እየዘመነች እና እያደገች በመምጣቷ የኅብረተሰቡም የጥንቃቄ ባሕል በዛው ልክ ማደግ አለበት የሚሉት ባለሙያው፤ ኮሚሽኑም ከተማዋን የሚመጥን አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እያደረገ መሆን ገልጸዋል፡፡

ከጥንቃቄ አልፈው ለሚያጋጥሙ አደጋዎችን ለመከላከል ከ10 ቅርንጫፎች በተጨማሪ በየካ ክፍለ ከተማ በቅርቡ አንድ አዲስ ቅርንጫፍ በመጨመር የቅርንጫፎቹን ቁጥር ወደ 11 በማሳደግ የመከላከል ሥራዎቹን አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተናግረዋል፡፡

አደጋ ሲያጋጥም ደርሰው ምላሽ የሚሰጡ ዘመናዊ ማሽነሪዎች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በአንድ ክፍለ ከተማ በአማካኝ ከሦስት እስከ አራት የሚሆኑ ማሽነሪዎች መኖራቸውንም ጠቁመዋል፡፡ ልዩ ልዩ የጤና እክል የገጠማቸውን ሰዎች የሚያግዙ በየማዕከሉ አምቡላንሶች መኖራቸውንም ገልጸዋል።

በቂ ሥልጠና የወሰዱ ባለሙያዎችም መኖራቸውን ተናግረው፤ ለባለሙያዎቹ የሥራ ላይ ሥልጠና በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገራት እንዲወስዱ እንደሚደረግም አመላክተዋል፡፡

ክረምቱ ከገባ እስከአሁን ድረስ ባለው ጊዜ በሰው ሕይወት ላይ የደረሰ አደጋ አለመኖሩን የሚናገሩት ባለሙያው፣ ጎርፍ በቁሳቁስ እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን ተናግረዋል፡፡

የዘንድሮ ክረምት ብዙ አደጋ ባለማጋጠም የተሻለ መሆኑን አመልክተው፤ ይህም አስቀድሞ በመከላከል ላይ የመሠራቱ ውጤት ነው ብለዋል፡፡

ኅብረተሰቡ የክረምት ወቅት በመሆኑ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ዝናብ ሊጋጥም እንደሚችል የብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ ትንበያ ያመላከተ በመሆኑ ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ስምምነቱ የሠላም ግንባታ ሥራዎችን ለማጠናከር የሚያስችል ነው

**አዲሱ ገረመው**




አዲስ አበባ፡- ኢፕድ እና የሠላም ሚኒስቴር አብረው ለመሥራት የተፈራረሙት የመግባቢያ ስምምነት የሠላም ግንባታና የአብሮነት እሴት ሥራዎች አጠናክሮ ለማሠራት እንደሚያስችል ተገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እና የኢፌዴሪ ሠላም ሚኒስቴር በተለያዩ ጉዳዮች አብረው ለመሥራት የሚያስችላቸውን የሁለትዮሽ ስምምነት ፊርማ ትላንት ተፈራርመዋል፡፡

በዚሁ ወቅት ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሳፍንት ተፈራ እንደገለጹት፤ የሀገር ግንባታ ዜጎች አዕምሮ ውስጥ የሚሠራ ነው፡፡ ሀገር የምትገነባውም በዜጎች አዕምሮና ልብ ውስጥ ነው፡፡ ይህ የሚመሠረተውም ሀሳብ ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ሆነ የሠላም ሚኒስቴር በዋናነት የሚያገናኛቸው ጉዳይ ዜጋ ላይ መሥራታቸው ነው፡፡ ስምምነቱም አቅምን አቀናጅቶ የተሻለ የሠላም ግንባታ ሥራዎችን ለማከናወን ያስችላል፡፡

ሁለቱም ተቋማት በሀገር ግንባታ ሥራ ተመሳሳይ ኃላፊነት እንዳለባቸው የገለጹት አቶ መሳፍንት፤ የሠላም ግንባታ በኮሙኒኬሽን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በታሪኩ ያካበታቸውን ልምዶች ተጠቅሞ እንደሚሠራም ተናግረዋል፡፡

ኢፕድ በኅትመት ሥራዎቹ ለረጅም ጊዜ ሀገር ሲገነባ እንደቆየ፤ ባሉት የኅትመት ውጤቶች በርካታ ሥራዎችን እየሠራ እንዳለ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ወደ ዲጂታል ዓለም እየገባ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ድርጅቱ “ስለ ኢትዮጵያ”ን ጨምሮ የተለያዩ ሁነቶችን በማሰናዳት ረገድም አቅሙን ማሳደግ እንደቻለም ጠቁመዋል፡፡ በእነዚህ ሥራዎች በሀገር ግንባታ ላይ የራሱን ዐሻራ ማሳረፍ መቻሉንም ነው የገለጹት፡፡

ስምምነቱ ሁለቱ ተቋማት ለየብቻቸው የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች የጋራ የማድረግ ትልም መሆኑን ጠቅሰው፤ ነባሩን አቅም በመጠቀምና በማሳደግ ሁለቱ ተቋማት የሚያቀራርቡና የወል ትርክት ላይ በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሠላም ታሪክ በፎቶና በጽሑፍ ኢፕድ ውስጥ ይገኛል በማለት፤ ይህንን በአግባቡ በመጠቀም ዜጋው የሠላም ሀብት እንዳለው እንዲያውቅ በተለያዩ ዓውደ ርዕይዎች እንዲያዩ ይደረጋል ብለዋል፡፡ የተለያዩ ሀገራዊ አንድነትንና አብሮነትን የሚያጠናክሩ፣ የፓናል ውይይቶች እንደሚኖሩ ከዚህ ባሻገር የተለያዩ ሥልጠናዎች እንደሚሰጡም አስታውቀዋል፡፡

የሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የመግባቢያ ስምምነቱ በተለይ የሠላም ግንባታና የአብሮነት እሴት ሥራዎች ላይ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ ኢፕድ ከዚህ ቀደም ሕዝቦች አንድ ላይ ተገናኝተው ስለ ሀገር እንዲነጋገሩ በማድረግ የጀመራቸው ሥራዎችና ሚኒስቴሩ በሚያደርጋቸው ሁነቶች ላይ የዜና ሽፋን በመስጠት እያደረገ ያለው ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

ሚኒስቴሩ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በብሔራዊ መግባባት፣ በአብሮነት፣ እንዲሁም የፌዴራል ሥርዓቱን ከማጠናከር አኳያ ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠራ እንዳለ የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ እነዚህን ተግባራት ከሚዲያ ጋር አብሮ መሥራት የምርጫ ጉዳይ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

ሀገራዊ፣ ቀጣናዊና አሕጉራዊ በሆኑ ትላልቅ መድረኮች ላይ ከዜና ሽፋን በዘለለ ሁነቶች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ ከኅትመት ሥራው ጎን ለጎን ተጨማሪ አቅም እየፈጠረ እየመጣ ካለው ኢፕድ ጋር አብሮ መሥራት ግድ የሚልበት ወቅት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የሠላም ሚኒስቴር በተለይ አዎንታዊ ሠላም ግንባታና አብሮነት ላይ እና የፌዴራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የተለያዩ የሚዲያ “ፕላትፎርሞችን” ይጠቀማል። ከተለያዩ ብዙኃን መገናኛዎች ጋር እየሠራም ይገኛል። ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በሚኖረው ግንኙነት በተለይ በኅትመቱ ዘርፍ አንጋፋ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ሥራዎች እስከታችኛው መዋቅር ማድረስና ዜጎች ስለ ሀገራቸው ኃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ሥራዎች በተለያዩ አማራጮች እንዲሄዱ ይደረጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በትውልድ ግንባታ ላይ በኢፕድ በቅርቡ የተጀመረውን የሕጻናት መጽሔትን ጨምሮ ዜጎች ከትምህርት ቤት ጀምረው እንዲታነጹ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ በጋራ እንደሚሠራ ተናግረዋል። ከዚህም ባሻገር በወሰን ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ለሀገር ግንባታ የሚያግዙ የጋራ ሥራዎች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡

ኢፕድ አሕጉራዊ መድረኮችን የሚመጥን ሥራ እየሠራ መሆኑን እናምናለን ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ተቋሙ ሰፋፊ የዶክመንተሪ ልምድ ያለው በመሆኑም ሰፋፊ ሥራዎች በጋራ እንደሚሠሩ፤ በሠላምና በሀገር አንድነት ላይ ያተኮሩ ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀት ሀገራዊ ግንባታ ላይ ጠንካራ ሥራዎችን እንደሚያከናውኑ አስታውቀዋል፡፡

ፕሬስ በራሱ የአብሮነት ቤት እንደመሆኑ አቅሙን ልንጠቀምበት ይገባል ነው ያሉት፡፡ ኢትዮጵያን በጽሑፍ ደረጃ ከ80 ዓመታት በላይ ታሪክ የያዘ ሲሆን፤ ይህንን መጠቀም ለዘላቂ ሀገራዊ አንድነት የሚጠቅም ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ሠላም ሚኒስቴር ኢፕድን እንደ ቁልፍ አጋር አድርጎ እንደሚያይ ጠቅሰዋል፡፡

የሁለትዮሽ ስምምነት የፊርማ ሥነ ሥርዓቱ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መሳፍንት ተፈራ እና በኢፌዴሪ ሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶክተር) መካከል ተፈጽሟል፡፡

# በአርአያነት የሚጠቀሰው ወጣት ማዕከል

**ነፃነት ዓለሙ**



**ዜና ሐተታ**

አሁን አሁን በመዲናችን አዲስ አበባ አዳዲስ የመዝናኛና የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች እየተስፋፉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ለነዋሪው የተለያየ ጠቀሜታ ከመስጠታቸው ባሻገር ወጣቱን ከአልባሌ ስፍራ ከመጠበቅ አኳያ ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ በከተማዋ ዋና ዋና ቦታዎች የሚገኙት እነዚህ የመዝናኛና የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆኑ በየአካባቢው የሚገኙ የወጣት ማዕከላትም ወጣቶች ጊዜያቸውን እንደየዝንባሌያቸው እንዲያሳልፉ በማድረጉ ረገድ የተሻለ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

እንደሚታወቀው የወጣት ማዕከላት በቋሚነት ለታዳጊዎችና ለወጣቶች የቤተመጽሐፍት፣ የስፖርትና የልዩ ልዩ መዝናኛዎች እንዲሁም የሥነተዋልዶ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር አሁን ላይ የተማሪዎች የእረፍት ጊዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከወጣት ማኅበራት ጋር በመተባበር ለሦስት ወራት በልዩ ልዩ ዘርፎች ሥልጠናዎችን እየሰጡ ያሉ የወጣት ማዕከላት አሉ፡፡

ከእነዚህም አንዱ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 ወጣት ማዕከል አንዱ ነው፡፡ ወጣት ማዕከሉ የተለያዩ ወጣትና ታዳጊዎችን በአይ ሲ ቲ፣ በተለያዩ የኪነ ጥበብ ዘርፎች ሥነጽሑፍ፣ ውዝዋዜና ትወና እንዲሁም በስፖርቱ ዘርፍ ውሹ፣ ቴኳንዶ፣ ቦክስ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እያሠለጠነ እንደሚገኝ የወረዳው ወጣት ማኅበር ሰብሳቢ አቶ ኤፍሬም ዳንኤል ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ኤፍሬም ገለፃ ወጣት ማዕከሉ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር በፈረቃ ከፋፍሎ በሳምንት ለሦስት ቀናት ሥልጠናዎቹን የሚሰጥ ሲሆን እንደመዝናኛ ደግሞ ቴኒስ፣ ጆተኒ እና ፑል የመሳሰሉትን በሥልጠናው ውስጥ ላሉ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ወጣቶችም ጭምር እንደ አንድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የወጣት ማኅበራቱ በወጣት ማዕከል ውስጥ ብቻ ሳይወሰኑ ከማዕከሉ ውጪም ተማሪዎችን ለቀጣይ ዓመት ትምህርት ከማዘጋጀት አንፃር በአካባቢው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የማጠናከሪያ ትምህርቶችን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለእረፍት የተመለሱ በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር እንደሚያስተምሩ እና በጎ ፍቃደኞችን በማሠልጠን በከተማዋ ጎዳናዎች ላይ የትራፊክ አገልግሎት እንዲሰጡ ዕድል መመቻቸቱን አቶ ኤፍሬም ገልፀውልናል፡፡

በወጣት ማዕከሉ የቤተመጽሐፍት አገልግሎት መስጠት ጋር በተያያዘም የንባብ ሳምንት እና የጥያቄና መልስ ውድድር በማዘጋጀት በተለይ ትምህርት ላይ ያሉ ታዳጊዎች እውቀታቸውን የሚያጎለብቱበት ዕድል እየፈጠረ እንዳለ ገልፀውልናል፡፡

ከዚህ ውጪ የሥነተዋልዶ ሥልጠናም ለታዳጊዎችና ለወጣቶች ግንዛቤ ከመስጠት አኳያ እንደ አንድ የክረምት መርሐ ግብር ተይዞ በማዕከሉ እንደሚሰጥ ገልፀው እነዚህን ሁሉ ሥልጠናዎች ክረምቱ ከመግባቱ በፊት እንደእቅድ ይዘው በስፋት ሠርተውበት ወደተግባር እንደገቡም አብራርተዋል። ነገር ግን እነዚህ ተግባራት ክረምት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ተጠናከሩ እንጂ አብዛኞቹ አገልግሎቶች ዓመቱን ሙሉ በወጣት ማዕከሉ የሚሰጡ መሆናቸውን ነግረውናል፡፡

ጥቁር አንበሳ TIKUR ANBESSA

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የቆዳና አባላዘር ሕክምና ትምህርት ፈር ቀዳጅ

**ሶሎሞን በየነ**

በዓለማችን በሳይንስ የተረጋገጡ ከሦስት ሺህ በላይ የቆዳ በሽታዎች እንዳሉ የቆዳና የአባላዘር ሐኪሞች ይጠቅሳሉ። ታዲያ ችግሩ በከፍተኛ ደረጃ ከሰሐራ በረሃ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ጎልቶ እንደሚስተዋል መረጃዎች ያሳያሉ። ከነዚህ ሀገራት ውስጥ ደግሞ ኢትዮጵያ አንዷ ናት። ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ለቆዳና ለአባላዘር በሽታ የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑ፤ የቆዳና የአባላዘር ሕክምና ባለሙያዎችን አስተምሮ የሚያፈራ ተቋም ለዘመናት አልነበረም።

በዚህም ሕክምናው በስፋት ይሰጥ የነበረው በጥልቀት ስለቆዳና አባላዘር ሕክምና ሥልጠና ባልወሰዱ ሐኪሞች ነበር። እንዲሁም ወደ ውጭ ሀገር ሄደው በዘርፉ ስፔሻላይዝድ አድርገው የመጡ በጣት የሚቆጠሩ ባለሙያዎች ወይም ሐኪሞች ቢኖሩም፤ እነዚህ ባለሙያዎች ከመዲናዋ ውጭ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍል ባሉ የጤና ተቋማት በባትሪ ተፈልገው አይገኙም ነበር።

ታዲያ ሁሌም በሕክምናው ዘርፍ አንድ እርምጃ ቀዳሚ የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፤ ችግሩን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የቆዳና የአባላዘር በሽታ ሕክምና ትምህርትን በ1998 ዓ.ም መስጠት እንደጀመረ የሚናገሩት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቆዳና የአባላዘር ሕክምና ክፍል ኃላፊና በሙያቸው ደግሞ የቆዳና የአባላዘር ስፔሻሊስት እንዲሁም ከቆዳ ጋር የተያያዙ የቆዳ አለርጂ ሐኪም ዶክተር አሕመድ መሐመድ ናቸው።

በሕክምናው ዓለም ከ30 ዓመት በላይ ወገናቸውንና ሀገራቸውን ያገለገሉት ዶክተር አሕመድ ስለ ቆዳና አባላዘር ሕክምና ክፍሉ አመሠራረት ታሪካዊ ዳራ እንዳብራሩት፤ "የቆዳና የአባላዘር ሕክምና ዓለም ከደረሰበት ደረጃ አንጻር የሕክምና አገልግሎቱን ለማሻሻል፣ ለማኅበረሰቡ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ካለው ሰፊ የሕክምና ፍላጎት አኳያ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ" በማሰብ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ዶክተር ዳኛቸው ሺበሺ እንዲሁም ከአለርት ሆስፒታል ዶክተር መንግሥቱ ኀለተወርቅ እና ዶክተር መስፍን ሁነኛው ትምህርት ክፍሉን ለማቋቋም ይነሳሉ።

የነዚህን በዘርፉ የሠለጠኑ ባለሙያዎች ሀሳብ በወቅቱ የነበሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና የሕክምና ፋኩሊቲ አመራሮች ተቀብለው ድጋፍ በማድረጋቸው፤ ሦስቱ የሕክምና ጠበብቶች ትምህርት ክፍሉን በ1998 ዓ.ም ለመመሥረት በቅተዋል። ሆኖም ትምህርት ክፍሉ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ቢቋቋምም የቦታ ጥበት በመኖሩ ሥልጠናውን በተቋሙ ለመስጠት አስቸጋሪ ነበር። በወቅቱ አለርት ሆስፒታል በዘርፉ ሥልጠናውን ለመስጠት የተሻለ አደረጃጀት ላይ ስለነበር፤ ከሆስፒታሉ ጋር የጋራ ስምምነት በመፈራረም እስካሁን ድረስ በስፋት ሥልጠናና የሕክምና አገልግሎቱ በዚያ እየተሰጠ ይገኛል።

ምክንያቱም አለርት ሆስፒታል ጥንት ሲቋቋም ለሥጋ ደዌ ሕሙማን ሕክምና መስጫ ተብሎ ነው። ሥጋ ደዌ ደግሞ አንድ የቆዳ በሽታ ነው። በሽታውም የሚታከመው በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዝድ ባደረጉ ሐኪሞች ነው። በመሆኑም ውጭ ሀገር ሄደው በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ሐኪሞች ይመደቡ የነበሩት አለርት ሆስፒታል ነው። ይህንን ተከትሎ የቆዳና የአባላዘር ታካሚዎች ለከፍተኛ ሕክምና ከአራቱም ማዕዘን ወደ ሆስፒታሉ ይላካሉ። ስለዚህ ታካሚዎች በብዛት ከመገኘታቸው ባሻገር ሰፊ ቦታ፣ ምቹ ሁኔታና ግብዓት አለርት ላይ አለ።

ከዚህ አንጻር በተግባር አስደግፎ ትምህርቱን ለመስጠት ትምህርት ክፍሉ ሥልጠናውን መስጠት የጀመረው በአለርት ሆስፒታል ነው። አሁንም 80 በመቶ ወይም በአብዛኛው የመማር ማስተማር እንዲሁም የሕክምና አገልግሎቱ እየተሰጠ የሚገኘው በአለርት ነው። ይህም ሲባል መማር ማስተማሩ ሙሉ ለሙሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የቆዳና አባላዘር ሕክምና ክፍል ነው የሚከናወነው።



ዶክተር አሕመድ መሐመድ፤

ነገር ግን የሕክምና አገልግሎቱን የሁለቱም ተቋም ባለሙያዎች በቅንጅት እየሰጡ ይገኛሉ። የጥቁር አንበሳ መምህራንና ሠልጣኞች በአለርት ያክማሉ። አለርትም በዘርፉ የራሱ ባለሙያ አለው። እነሱም የሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። ስለዚህ የሁለቱም ተቋም ባለሙያዎች የተቋም ልዩነት ሳይበግራቸው ወገንን የማገልገል አንድ ዓላማ ሰንቀው በጋራ ወይም በቡድን የሕክምና አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ።

ትምህርት ክፍሉ በዚያም ተመላላሽ ታካሚዎችን የሚያክምበት ወደ ስድስት የሚደርሱ ክፍሎች እንዲሁም ተኝተው የሚታከሙ በሽተኞችን የሚያክምበት በርከት ያሉ አልጋዎች አሉት። ስለዚህ የጥቁር አንበሳ ባለሙያዎች በአለርት ሆስፒታል ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን ለአያሌ ሕመምተኞች የሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። በተመሳሳይ በጥቁር አንበሳ ግቢም ቢያንስ በቀን ከ30 እስከ 40 ለሚደርሱ ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጥ ይናገራሉ።

አንድ ጠቅላላ ሐኪም በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዝድ ለማድረግ ሦስት ዓመት እንደሚወስድበት ዶ/ር አሕመድ ጠቅሰው፤ ትምህርት ክፍሉ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ በ1998 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹን ሠልጣኞች ተቀብሎ፤ በሀገር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አሠልጥኖ አስመርቋል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ ከ10 እስከ 12 ሠልጣኞችን ተቀብሎ ያሠለጥናል።

በተመሳሳይ በየዓመቱ ይህንኑ ያህል ቁጥር ያላቸው ሠልጣኞችን እያስመረቀ ይገኛል። አሁን ላይም በትምህርት ክፍሉ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ዓመት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ 30 ሠልጣኞች አሉ። ስለዚህ በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዝድ የሚያደርጉ ሐኪሞችን በማሠልጠን ቀዳሚው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ነው።

ትምህርት ክፍሉ የዛሬ 18 ዓመት ሥልጠናውን በሀገር ውስጥ መስጠት ሲጀምር፤ በሀገሪቱ በዘርፉ ስፔሻላይዝድ ያደረጉ ወይም የሠለጠኑ ባለሙያዎች ከ20 የማይበልጡ ነበሩ። እነዚህ ባለሙያዎቹ አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ተወስነው ነበር አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት። ሆኖም ትምህርት ክፍሉ ከተመሠረተ በኋላ ባለሙያዎችን በማፍራት ረገድ በተጫወተው ሚና፤ ዛሬ ላይ በመላ ሀገሪቱ በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዝድ ያደረጉ 200 የሚደርሱ የቆዳና አባላዘር ሕክምና ሐኪሞች ይገኛሉ። እነዚህ ባለሙያዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የሕክምና አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ።

ሌላው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በቆዳና አባላዘር ሕክምና ትምህርት ፈር ቀዳጅ ከመሆኑ ባሻገር፤ በሌሎች መሰል የማስተማሪያ ሆስፒታሎችና የሕክምና ትምህርት ቤቶች የቆዳና አባላዘር ሕክምና ትምህርት ክፍሎች እንዲቋቋሙ መሠረት የጣለ ነው። በዚህም አሁን ላይ በሀገሪቱ ከጥቁር አንበሳ ውጭ አምስት ተቋማት ላይ በዘርፉ የሕክምና ትምህርት ክፍሎች ተቋቁመው፤ ሠልጣኞችን ተቀብለው አስተምረው ለማስመረቅ በቅተዋል።

በሀገሪቱ ባሉ የማስተማሪያ ሆስፒታሎችና የሕክምና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የቆዳና አባላዘር ሕክምና አገልግሎት እና ትምህርት የሚሰጡ ሐኪሞችና መምህራኖች አብዛኞቹ ከጥቁር አንበሳ ሠልጥነው የወጡ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

በቆዳና አባላዘር ሕክምና ስፔሻላይዜሽን ሙያ ከ19 ዓመታት በላይ ልምድ ያላቸው ዶ/ር አሕመድ፤ ተቋሙ በዘርፉ በሚሰጠው የሕክምና አገልግሎትና ሥልጠና ከሌሎች መሰል ተቋማት ለየት ከሚያደርገው ነገር አንዱ፤ በዘርፉ የዳበረ ልምድ፣ ክህሎትና እውቀት ያላቸው ባለሙያዎች መገኛ መሆኑ ነው። ለአብነት እንደሀገር ውጭ ሀገር ሂደው ሠልጥነው የመጡ ሁለት የቆዳ ሥነ-ደዌ ስፔሻሊስት ሐኪሞች ብቻ ነበሩ። ከሁለቱ አንዱ ባለሙያ የሚገኘው በጤና ሳይንስ ኮሌጁ ነው። ስለዚህ ይህ ባለሙያ በሌሎች ጤና ተቋማት የማይሰጡ የተለዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

ሌላው በቆዳና አባላዘር ቀዶ ሕክምና ውጭ ሀገር ሂደው ስፔሻላይዝድ አድርገው የመጡ ሁለት ባለሙያዎች በትምህርት ክፍሉ ይገኛሉ። በሀገሪቱ ባሉ የመንግሥት ጤና ተቋማት እነዚህ ባለሙያዎች ያሉት በዚህ ትምህርት ክፍል ብቻ ነው። ስለዚህ በተመሳሳይ እነዚህ ባለሙያዎች በሌሎች የመንግሥት ጤና ተቋማት የማይሰጥ የቆዳና አባላዘር ቀዶ ሕክምና አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።

እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ በሕፃናት ቆዳ ስፔሻሊስት ውጭ ሀገር ሂዳ ሠልጥና የመጣች ባለሙያ እንዳለች ይጠቅሳሉ። በኢትዮጵያ ይቺ አንድ ለእናቷ ብርቅዬ ባለሙያም የምትገኘው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ውስጥ ነው። ከዚህ በተጨማሪም እሳቸውም ዶ/ር አሕመድ በቆዳ አለርጂ ሕክምና ውጭ ሀገር ሂደው አጭር ሥልጠና ወስደው በመምጣት፤ ሥልጠናውን እንዲሁም ሕክምናውን በሀገር ውስጥ ለወገናቸው እየሰጡ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

ይሁ ሁሉ ስኬት የተመዘገበው ነገሮች አልጋ በአልጋ ሆነው ሳይሆን ባለሙያው ሕዝብና ሀገርን ለማገልገል ባለው ቁርጠኝነት ነው የሚሉት ዶክተር አሕመድ፤ ትምህርት ክፍሉ ከዚህ በላይ አገልግሎትና ሥልጠና እንዳይሰጥ ወድረው ከያዙት ተግዳሮቶች ውስጥ የመጀመሪያው ለቆዳና አባላዘር ሕክምና የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ ነው። ባለው የተዛባ አመለካከት እስካሁንም ቅድሚያ ከተሰጣቸው የሕክምና ዘርፎች ተርታ አልተቀመጠም።

ነገር ግን አንድ ሰው ምንም ይታመም ምን በወቅቱ ሕክምና ካላገኘ ሕይወቱ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ጥርጥር የለውም። አንድ ሰው ቆዳና አባላዘር በሽታ ይታመም ወይም ሌላ ሕመም ይታመም ሁሉም እኩል መታየት አለባቸው። ስለዚህ ቆዳና አባላዘር በሽታን ከሌለው በሽታ እኩል ማየት ይገባል። እኩል ትኩረት ሊሰጠውና ለዘርፉ ሕክምና የሚያስፈልጉ ግብዓት ሟሟያ በቂ በጀት ሊመደብለት ይገባል።

ሌላው የቦታ ጥበት አንዱ ዋናኛ ተግዳሮት ነው። የቦታ ጥበት በመኖሩ ሥልጠናና የሕክምና አገልግሎቱ እስካሁን ድረስ በስፋት እየተሰጠ ያለው በሌላ ተቋም ነው። እንዲሁም የበጀት ውስንነት በመኖሩ፤ የተሻለ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ ማቴሪያሎች፣ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ግብዓቶችን ማሟላት አልተቻለም። ይሁን እንጂ ባለው የበጀት እጥረት ቅድሚያ ለሌሎች ዘርፎች በመሰጠቱ ክፍሉ ያቀረበው ጥያቄ እምብዛም ምላሽ አላገኘም።

እንደዶክተሩ ገለፃ እነዚህ እግር ከወርች ጠፍረው አላራምድ ያሉ ተግዳሮቶች በመኖራቸው ትምህርት ክፍሉ ያለበት ደረጃ መድረስ አልቻለም። ሆኖም እንደ ትምህርት ክፍሉ ያሉ እንቅስቃሴዎች የተሻሉ ናቸው። ያሉ ችግሮችን ተቋቁሞ ባለው ነገር የተሻለ ሕክምናና ሥልጠና እየሠጠ ይገኛል። ከዚህ በላይ ግን የሚመለከታቸው አካላት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው የቦታ ጥበቱ፣ የበጀት ችግሩ ተቀርፎ፤ በአንጻሩ ደግሞ ግብዓት፣ ማቴሪያል እንዲሁም ዘመን አፈራሽ ቴክኖሎጂዎች ተሟልተው ከቀረቡ፤ በትምህርት ክፍሉ የበቁ ባለሙያዎች ስላሉ ከአደጉ ሀገራት ያልተናነሰ ሕክምና በዘርፉ መስጠት ይችላሉ። ይበልጥ ሕክምናውን ማዘመንና ተገልጋዮችንም ማርካት ይቻላል።

እንዲሁም የቆዳና አባላዘር ሕክምና የሰብ-ስፔሻሊስት ሥልጠና እስካሁን ድረስ ባለሙያዎች ውጭ ሀገር እየሄዱ ነው የሚሠለጥኑት። ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከተቀረፉ የሰብ-ስፔሻሊስት ሥልጠናውን በሀገር ውስጥ ለመጀመር የተያዘውን እቅድ በቅርቡ ወደ ተግባር በመቀየር፤ በስፋት ሠልጣኞችን በሀገር ውስጥ በማሠልጠን በከፍተኛ ደረጃ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ማፍራት ይቻላል። ከዚህ ባሻገር ሀገሪቱ ባለሙያዎችን ለማሠልጠን የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ወጪ ይቀርፋል።

በጥቅሉ ትምህርት ክፍሉ ያሉበት ተግዳሮቶች ከተቀረፉለትና ምቹ ሁኔታዎች ከተፈጠሩለት በዘርፉ በሚሰጠው ሕክምና ሌሎች የአደጉ ሀገራት የደረሱበት ደረጃ ለመድረስና የላቀ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ታትሮ እየሠራ ነው። እየሰጠ ያለውን የስፔሻሊቲ ሥልጠና አጠናክሮና ጥራቱን አስጠብቆ ከማስቀጠል ባለፈ በመጪው ጊዜ የሰብ-ስፔሻሊቲ ሥልጠናን ለመጀመር ግብ አስቀምጦ፤ ግቡን ለማሳካት እየሠራ እንደሚገኝ ዶ/ር አሕመድ አስረድተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጉባኤው ሕገወጥነት ከሚፈጥረው ሁከት እና ግርግር ለማትረፍ የሚደረግ ጥረት ነው!

ባለንበት ዘመን የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ሕልውና የሚወሰነው ለሕግ እና ለሕጋዊ ሥርዓት ካለው ተገዥነት ነው። በተለይም በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በሚገኙ ሀገራት ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሥርዓቱ ግንባታ ካላቸው የማይተካ አበርክቶ አኳያ ለሕግ እና ለሕጋዊ ሥርዓት የመገዛታቸው እውነታ አጠቃላይ ከሆነው የሀገር ዕጣ ፈንታ ጋር የሚቆራኝ ነው።

ይህንን እውነታ በአግባቡ ተረድቶ፤ እለታዊ በሆነው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተፈጻሚ ማድረግ ያልቻለ የፖለቲካ ድርጅት፤ የትኛውም አይነት የሕዝብ ውክልና እንዳለው አድርጎ የማሰብ ዕድሉ ቢኖረውም፤ ውክልናው በሕዝብ ውስጥ ሕገወጥነትን ከማስፈን ባለፈ ሊያመጣው የሚችለው ሕዝባዊ ተጠቃሚነት አይኖርም።

ከሕግ የበላይነት ያፈነገጠ የፖለቲካ መስመር አንድም ራስን ከሕግ በላይ አድርጎ ከማሰብ ያልተገባ እብሪት፤ አለበለዚያም ሕገወጥነት በሚፈጥረው ሁከት እና ግርግር የራስን ድብቅ ፍላጎት ለማሳካት የሚደረግ ጊዜ ያለፈበት፤ የዘመኑን ትውልድ የማይመጥን፤ የሚያሳንስ እና ላልተገባ ችግር የሚያጋልጥ ነው።

በተለይም በድህነት እና በኋላ ቀርነት ውስጥ በሚኖሩ ሕዝቦች ውስጥ እንዲህ አይነቱ ችግር ተደጋግሞ የመከሰቱ እውነታ ፤ የሕዝቦቹን ዛሬን ከማበላሸት አልፎ፤ ነገዎቻቸውን የግጭት ጽልመት በማልበስ፤ ትውልዶች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዳይወስኑ የሚያደርግ፤ የሚያስከፍላቸውም ዋጋ ተስፋቸውን እስከመናጠቅ የሚደርስ ነው ።

ይህ እውነታ እንደሀገር እኛ ኢትዮጵያውያንን ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል ያስገደደን፤ ዛሬም ድረስ እንደ ጥላ እየተከተለን ላለው እና አንገታችንን ለሚያስደፋን ድህነት እና ኋላቀርነት በዋንኛነት ተጠቃሽ ነው፤ ነገን ተስፋ አድርገን ለጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ መነቃቃትም ፈተና የሆነ ነው።

በፖለቲካ ፓርቲ እና በነፃ አውጪነት ስም ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት እንደ ሀገር ብዙ ያልተገቡ ዋጋ ለመክፈል በተገደድንባቸው የግጭት አዙሪቶች ውስጥ አልፈናል። በዚህም የተለያዩ ትውልዶች እስከ ተስፋቸው ተገንዘው ተቀብረዋል። በመቃብራቸው ላይ የመሠረትነውም የፖለቲካ ሥርዓት የቀጣይ ትውልዶችን ተስፋ በልቷል።

በቅርቡ እንኳን የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተወካይ ነኝ የሚለው ሕወሓት ከለውጡ ማግስት፤ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ወደ ሥልጣን ከመጣው መንግሥት ጋር የነበረውን ልዩነት በኃይል ለመፍታት የሄደበት ያልተገባ መንገድ ሀገርን፤ በተለይም የትግራይን ሕዝብ ያስከፈለው ዋጋ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ለማስታወስ አይከብድም።

ለራሱ፣ ለቤተሰቡ እና ለሀገር ተስፋ የነበረን ትውልድ ለሞት እና ለአካል መጉደል፤ ከፍተኛ መጠን ያለው የሀገር ሀብት ለውድመት ዳርጓል። መንግሥት ችግሩን ለዘለቄታው በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት በወሰደው ርምጃ ችግሩ በሠላም ስምምነት ባይፈታ ኖሮ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ተጨማሪ ጥፋት መገመት ቀላል ነው።

ሕግ እና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓትን በማክበር ላይ የተመሠረተው የሠላም ስምምነቱ፤ ከሁሉም በላይ ለትግራይ ሕዝብ ሠላም ማስፈን ያስቻለ፤ ሕዝቡን ግጭት ከሚፈጥረው ሞት፣ የአካል ጉዳት፣ ስደት እና የሥነልቦና ቀውስ የታደገ ነው። ሕዝቡ ስለ ልማት አስቦ እንዲንቀሳቀስ የተሻለ መነቃቃት የፈጠረም ነው።

የፌዴራል መንግሥት የሠላም ስምምነቱን ተከትሎ የወሰዳቸው ርምጃዎች፣ የትግራይ ሕዝብ ወደ ቀደመ ሕይወቱ እንዲመለስ ከማስቻል ባለፈ፣ ቀደምት ችግሮች ተመልሰው የግጭት ምንጭ እንዳይሆኑ ቀዳዳዎችን መድፈን ያስቻለ ነው። በሕወሓት በኩል የተስተዋሉ መጓተቶች እና ግጭት ቀስቃሽ ትንኮሳዎችን በሆደ ሰፊነት ያስተናገደም ነው ።

ለሠላም ካለው ቀናዒነት የመነጨው የፌደራል መንግሥት እንቅስቃሴ፤ ብዙ መጕረባበጦችን ለማለፍ የተገደደ ቢሆንም ፤ በተጨባጭ የትግራይ ሕዝብ ዋነኛ ፍላጎት የሆነውን የሠላም እና የልማት ጥያቄ በመመለስ ሂደት ውስጥ የጎላ አስተዋፅዖ አበርክቷል። በሕዝቡም ዘንድ አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል ።

ይህም ሆኖ ግን ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በላይ የትግራይ ሕዝብ ብቸኛ ተጠሪ አድርጎ ራሱን የሚቆጥረው ሕወሓት ፤ በነዚህ ዓመታት ውስጥ በትግራይ ሕዝብ ስም በሀገርም ሆነ በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጠራቸው ምስቅልቅሎች ምን ያህል ሀገር እና ሕዝብን ዋጋ እንዳስከፈሉ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ቡድኑ ትናንት በፈጠረው ስህተት የትግራይ ሕዝብ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን እስከ ተስፋቸው ለመቃብር ዳርጓል ፤ የዚህ ቡድን አንዳንድ የአመራር አባላት ከትናንት ስህተታቸው መማር አቅቷቸው ዛሬ ላይ በልጆቹ መቃብር ላይ ቆመው ለሕግ እና ለሕጋዊ ሥርዓት ደንታ ቢስ ስለመሆናቸው በተግባር እየዘመሩ ነው።

ይህ የቡድኑ አንዳንድ የአመራር አባላት እየሄዱበት ያለው መንገድ እንወክለዋለን የሚሉት የትግራይ ሕዝብ የዘመናት እና የትውልዶች ፍላጎት/ምኞት የሚጻረር፤ በየወቅቱ ለትግራይ ሕዝብ እውነተኛ ፍላጎት ሰማዕት የሆኑ የሕዝብ ልጆችን የመስዋዕትነት ዋጋ የሚያረክስ እና የሚያሳንስ ነው ።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትሩ ለገሠ ቱሉ (ዶክተር) በይፋዊ ማኅበራዊ ሚዲያ ገጻቸው "በየትኛውም የዓለም ጥግ ያለ ሀገር የሚመራው በሕግና በሥርዓት ነው። ሕግና ሥርዓት ከማንኛውም ሰው፣ ተቋም፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ ቡድን፣ ስብስብ በላይ ነው። እነዚህ ሁሉ ከሕግ እና ሥርዓት በታች ናቸው። ሕግና ሥርዓትን አክብሮ የማይንቀሳቀስ የትኛውም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ግቡ ጥፋት ነው፡፡

የሕወሓት ያለፉት ዓመታት የግትርነት ባሕሪም የዚሁ ምሳሌ ነው። ሕወሓት ደጋግሞ እንደመሸሸጊያ የሚያነሳው የፕሪቶሪያ ስምምነት የፌዴራል ተቋማትን አሠራሮች፣ ሕጎችና አካሄዶች በጥብቅ ሊያከብር ግዴታ ጥሎበታል። ቀድሞ የገባውን ግዴታ ሲሸራርፍ የመጣው ሕወሓት ዛሬ በተጨባጭ ተግባር ደምስሶታል፡፡ ድርጊቱ የትግራይ ሕዝብ ያገኘውን አንጻራዊ ሠላም እንደመንጠቅ ይቆጠራል፡፡ አንዴ፣ ሁለቴ፣ መሳሳት ያለና የነበረ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ተመሳሳይ ስህተት ሦስቴ መፈጸም ግን የመጨረሻው የጥፋት መንገድ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ብቸኛው ተጠያቂ ራሱ ይሆናል" ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ሕወሓት እየጓዘበት ያለው ከሕግ እና ከሕጋዊ ሥርዓት ያፈነገጠ መንገድ በየትኛውም መመዘኛ ትክክል ያልሆነ፤ ከቀደመ ስህተት ያልተማረበት፤ ተጨማሪ ክፍተት እና ስህተቱ ለሚያስከፍለው ያልተገባ ዋጋ ደንታ ቢስ የመሆን ማሳያ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከትግራይ ሕዝብ ፍላጎት በፍጹም ያፈነገጠ፤ ሕገወጥነት ከሚፈጥረው ሁከት እና ግርግር ለማትረፍ የሚደረግ ጥረትም ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ውጤቱ ምንም ይሁን ተጠያቂነት ሊኖር ይገባል!

**ብርሃን ፈይሳ**

በርካታ ድራማዊ ክስተቶችን ሲያስተናግድ የቆየው 33ኛው የፓሪስ ኦሊምፒክ ትናንት ተጠናቋል። ከመክፈቻ መርሐ ግብሩ አንስቶ ተቃውሞ ያስተናገደው የፓሪስ ድግስ በሳምንታት ቆይታው አስገራሚ፣ ያልተጠበቁ፣ አስደሳች እንዲሁም አሳዛኝ ክስተቶችን አሳልፏል። በኦሊምፒኩ ተካፋይ ከነበሩ ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም አነጋጋሪ የሆነ የኦሊምፒክ ተሳትፎዋን ከተለመደ ውጤት ርቃ በአንድ ወርቅና ሦስት የብር ሜዳሊያ አጠናቃለች።

ከኦሊምፒኩ አስቀድሞ ከነበረው የዝግጅት ወቅት አንስቶ አለመግባባትንና እሰጣ ገባን ሲያስተናግድ የቆየው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በፓሪስም ከምንጊዜውም በላይ የቁልቁለት መንገድ ተጉዟል። ዘመን በማይሽራቸው ድንቅ አትሌቶቿ በኦሊምፒክ የከበረችው ኢትዮጵያ ፓሪስ ላይ በውጤት አንሳ ታይታለች። በዚህም አትሌቲክስን የክብሩ መገለጫ ያደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከፍቷል።

በዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ድል መታወቂያቸው የሆኑ ብርቱ አትሌቶቻችን በአመራሩ ንትርክ የደረሰባቸው የሥነልቦና ጫና በራስ መተማመን ሲርቃቸውና ከለመዱት ውጤት ሲነጣጠሉ ተመልክተናል። ዓለም ቆሞ ያጨበጨበላቸው አንጋፋ አትሌቶቻችንም ክብራቸውን በማይመጥን ደረጃ ቦታ አጥተው የሕግ ያለህ ማለታቸውን ታዝበናል።

የስፖርት ቤተሰቡ ከመነሻው ሲተገበሩ የቆዩ ሕገወጥ ተግባራትን ለአትሌቶች ሞራል ሲባል ተመልክቶ ማለፍን ቢመርጥም ጥፋት ጥፋትን እየወለደ በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። በብርቱ አትሌቶቻችን ጥረት፣ ላብ እና ደም የተገነባው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ክብር፣ በጥቅም በተሰባሰቡ ሰዎች መናዱ የብዙዎችን ልብ ሰብሯል።

በዝግጅት ወቅት በኦሊምፒክ ዕጩዎች ምርጫ ላይ ብርቅዬ አትሌቶችን በማሳዘን የጀመረው ጥፋት ዕውቅና በሌለውና በድብቅ በተካሄደው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ምርጫ ነበር የቀጠለው። ይህ ሁኔታ መፍትሔ እንዲያገኝ ለሚነሱ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ከመስጠት ይልቅ እያድበሰበሱ በማለፍ እንዲሁም ስፖርቱን ለሚመራው መንግሥታዊ አካል ባለመታዘዝ ሁኔታዎች እንዲወሳሰቡና ጥፋቱ እንዲገዝፍ አድርጓል። ኦሊምፒኩ ከተጀመረ በኋላም እንደ ሠንሠለት እየተቀጣጠለ የሄደው ዝርክርክ አሠራር ሀገርን ለውጤት ቀውስ ዳርጓል።

የማይናወጥ የኢትዮጵያዊነት ስሜትን በመገንባት ስለ ግል ጥቅም ሳይሆን ስለ ሃገር ክብር የሚቆሙ ምርጥ አትሌቶችን ያፈራው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከፈረሰ በኋላ ስፖርቱ በማይገባው መንገድ እየተጓዘ ይገኛል። በተነጣጠለ ሁኔታ በግል አሠልጣኝ ተዘጋጅቶ ሃገርን መወከል ለውጤት መጥፋት ምክንያት መሆኑን ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ቢናገሩም ጆሮ የሰጣቸው ግን የለም።

በራሳቸው መንገድ ሲዘጋጁ የቆዩ አትሌቶችን ሰብስቦ በአንድነት እንዲወዳደሩ መደረጉ ውጤቱን በግልጽ እያሳየ ይገኛል። ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብር ሲሉ ከራሳቸው ይልቅ የሃገራቸው ልጅ የሚያስቀድሙ፣ የሚደጋገፉ፣ የሚተባበሩና በአንድነት ስሜት ለተፎካካሪዎቻቸው ራስ ምታት የሚሆኑ አትሌቶች እንደ ደመና እየራቁ፤ የኢትዮጵያውያን የኦሊምፒክ ተሳትፎም ውበትና ለዛውን እያጣ መጥቷል።

ከታመመ ዓመታትን በተሻገረው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ መድኃኒት ከማቀበል ይልቅ ቁስሉ ላይ እንጨት መስደድን ሥራዬ ብለው የተያያዙ ሰዎች አሁንም የስፖርቱ ነቀርሳ ሆነው ወደ ሞት እያንደረደሩት እንደሚገኙ ፓሪስ ላይ ቁልጭ ብሎ ታይቷል። ከአራት ዓመት በፊት በተመሳሳይ ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ የተፈጠሩ ስህተቶችና ጥፋቶች ተገቢውን መፍትሔ ሳያገኙ ነገሮች ባሉበት መቀጠላቸውም በጠራራ ፀሐይ ሃገር ስትዋረድ በግልጽ እንድንመለከት አድርጎናል።

ነገሮች «ስትሄድ እንቅፋት የመታህ ድንጋይ ስትመለስ ካገኘህ ...» እንደሚለው አባባል እየሆኑ፤ ኢትዮጵያን ባሳነሰው የቶኪዮ ኦሊምፒክ ዋና ተዋንያን በፓሪስም እንዲቀጥሉ ዕድል መስጠቱ በራሱ ግራ አጋቢ ነው። በመንግሥት በኩል ይህ ሁሉ ምስቅልቅል እንዲሆን መተውና እየሆነ ባለው ነገር ጣልቃ ያለመግባት ሕዝቡን ጥያቄ ውስጥ እየከተተውም ነው።

ከዚህ ቀደም የተደረጉ ሕገወጥ ተግባራት መቋጫ ሳያገኙ በእንጥልጥል መቅረታቸው የልብ ልብ የሰጣቸው የስፖርቱ አመራሮች አሁንም ነውራቸውን በግልጽ ከማሳየት ወደኋላ አላሉም። ስፖርቱን የሚመራውን የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ንቆ ከመንግሥትና ከሕዝብ በጀት እንዲለቀቅ ማድረግና ድጋፍ ማግኘት አሠራሩን ጥያቄ ውስጥ አይከትም? መንግሥትስ ይህን ሁሉ ጥፋት ሠርቶ የመጣውን የስፖርት አመራር እያባበለ ሊቀጥል አይገባም።

ከተሳታፊ አትሌቶችና ከሚመለከታቸው ሰዎች በእጥፍ የሚበልጡ ልዑካን ፓሪስ ተጉዘዋል። አመራሩ ቤተሰብና ዘመድ አዝማዱን አስከትሏል። ይህንን እጅግ አስከፊ ያደረገው ደግሞ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው የሄዱ አካላት በሚጠበቅባቸው ስፍራ አለመኖርና አትሌቶች የሚፈልጉትን አገልግሎት በማጣት መጉላላታቸው ነው። አሠልጣኞችንና ውድድራቸውን የጨረሱ አትሌቶችን ማዋከብና በፍጥነት ወደ ሀገር እንዲመለሱ በማድረግ ቦታ የማሸጋሸጉንም ተግባር ከሰሞኑ የታዘብነው ጉዳይ ነው።

የክልል ስፖርት ቢሮ ኃላፊዎችና የስፖርት ማኅበራት የሥራ አስፈጻሚዎች በሙሉ ጉዞ ማድረጋቸው የልምድ ልውውጥን ሽፋን ቢያደርግም እንኳን ተቀባይነት ያለው አይደለም። ኢትዮጵያ ከአትሌቲክስ ባለፈ በቦክስ፣ በብስክሌት እና እግር ኳስ ኦሊምፒክ ላይ በተሳተፈችባቸው ዘመናት ሳይቀር እጅግ የተመጠነ ቁጥር ያላቸው የኦሊምፒክ ኮሚቴ ተወካይ፣ የቡድን መሪዎች፣ በየስፖርቱ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ አሠልጣኞች እና የሕክምና ባለሙያዎች ነበሩ ከተወዳዳሪዎች ጋር የሚጓዙት።

ከኦሊምፒኩ አስቀድሞ ኦሊምፒክ ኮሚቴው በሰጠው መግለጫ ላይ ከመገናኛ ብዙኃን ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ከልዑካን ጋር የተያያዘ ነበር። በዚህም ወቅት የኦሊምፒክ ኮሚቴው ፕሬዚዳንት የሰጡት ምላሽ «ሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብስ ቢጓዝ ምን አለበት» የሚል ነበር። ይህ አሳፋሪ ምላሽ በድህነት ውስጥ ለምትዳክርና ከፍተኛ በሆነ የውጪ ምንዛሪ እጥረት ውስጥ ያለችን ሃገር ሁኔታ ያለማገናዘብ ነው። የጉዞ ሁኔታ ከአቅም ጋር የሚያያዝ ብቻም ሳይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውና በቀጥታ የሥራ ኃላፊነት ያላቸውን የሚያካትት ነው። ባይሆንማ በኢኮኖሚ አቅማቸው የፈረጠሙ ሃገራት ሕዝባቸውን ፓሪስ ላይ እንዲከትም ባደረጉ ነበር።

እንዳለፈው ጊዜ ሳይሆን በግልጽ የጉዞ ሪፖርት፣ ከውጤት ጋር በተያያዘ አስቀድሞ ከታቀደው የሜዳሊያ ቁጥር አንጻር ምን ያህሉ ተሳክቷል የሚለውን እስከ ምክንያቱ (ለኢትዮጵያ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ብቻውን ግብ አለመሆኑን ልብ ይሏል)፣ የገቢ እና ወጪ ኦዲት እንዲሁም ከጉዞ አስቀድሞ የነበሩ አለመግባባቶችንና በኦሊምፒኩ ወቅት ሲነሱ የነበሩ ጉዳዮች ላይ በሚገባ የተብራራ ምላሽ ሕዝቡ ይፈልጋል። ለሕግ የበላይነት የቆመው መንግሥትም ኃላፊነት የሰጠው የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር በምን ሁኔታ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንዳልቻለና በበላይነት የሚመራው የስፖርት ማኅበራት አልታዘዝ እንዳሉት መጠየቅ ይገባዋል።

ስፖርት ሃገሪቷ ከፍተኛ ወጪ የምታደርግበትና ምናልባትም በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድልን የፈጠረ አንድ ዘርፍ ነው። መንግሥትም ይህንን በመረዳት በመላ ሃገሪቷ ታላላቅ የስፖርት ፕሮጀክቶች ላይ ሃብቱን እያፈሰሰ ይገኛል። የስፖርት ቱሪዝምን በማሳደግ ከዘርፉ ከፍተኛ ገቢ ለማመንጨት በማሰብም በሃገራዊ የቱሪዝም መስሕቦች ውስጥ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከማካተት ጎን ለጎን የውድድር ዕድሎችንም እየፈጠረ ይገኛል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ይህንኑ ዘርፍ ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ስመጥር የስፖርት ሰዎችን በመጋበዝ ጭምር ስፖርቱን በአዲስ መንገድ ለማነቃቃት እየተገበሩ ያሉትን ሥራም በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው።

ይህ ዓለምን በማንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ግዙፍ ዘርፍ ለሃገራት የገቢ እንዲሁም የገጽታ ግንባታቸው ምንጭ ሆኗል። ኢትዮጵያን በበጎ ያስጠራት አትሌቲክስም ባለውለታዋ ነው። ይህንን መልካም ዕድል መጠቀም ሲገባ በየአራት ዓመቱ በመሰል አሳፋሪ ተግባራት የሃገርን ገጽታ ማጠልሸት፣ ሕዝቡን ማስከፋት እንዲሁም ከመንግሥት ካዝና የሚወጣን ገንዘብ በኃላፊነት አለመጠቀም ሊያስጠይቅ ይገባል። በመሆኑም መንግሥት የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳትና ሂደቱን በመመርመር ሳይውል ሳይድር በጥፋተኞች ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል።

# በመዲናዋ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢኮኖሚ ዞን ግንባታን አስጀምረናል ብለዋል።

በመዲናዋ የሚገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶች የነገዋን የአዲስ አበባ መልክ የሚቀይሩና ለኑሮ ምቹ የሚያደርጉ መሆናቸውንም ገልጸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ መንግሥት አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስ እና አበባ ለማድረግ በርካታ የልማት ሥራዎችን እያከናወነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሦስት አሠራሮችን እንደሚከተል ጠቅሰው፤ አንደኛው በመንግሥትና በግል አጋርነት የሚለሙ ሥራዎችን በአብነት አንስተዋል፡፡

ግንባታው የተጀመረው የ'አዲስ ቱሞሮ' ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ፕሮጀክት ለዚህ ማሳያ መሆኑን አንስተው፤ ይህና ሌሎች መሰል ፕሮጀክቶችም የነገዋን የአዲስ አበባ መልክ የሚቀይሩና ለኑሮ ምቹ የሚያደርጉ ስለመሆናቸው አብራርተዋል፡፡

ሌላኛው ሥራ በመንግሥት የሚከናወነው የኮሪደር ልማት መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኮሪደር ልማት በሁሉም አካባቢዎች ፍትሐዊና ተመሳሳይ ልማት እንዲኖር ያስችላል ብለዋል፡፡

በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለማስተሳሰር ሚናው የጎላ መሆኑንም አመልክተው፤ በግሉ ዘርፍ የሚከናወነው ሥራም ከተማዋን ለመቀየር የሚያግዝ ሦስተኛው አሠራር መሆኑን ጠቅሰው፤ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑንም አፅንዖት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

የከተማዋ ነዋሪዎችም በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎችን ከመጠቀም ባለፈ በባለቤትነት እንዲን ከባከቡና እንዲጠብቁ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል፡፡

በተለምዶ ጎተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገነባውን የ'አዲስ ቱሞሮ' የኢኮኖሚ ዞን ፕሮጀክት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከቻይና ኮሙኒኬሽን ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር እንደሚያከናውኑት ተገልጿል፡፡

ግንባታውም የመኖሪያ ቤትን ጨምሮ ሞሎች የንግድ ማዕከላትና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ያካተተ መሆኑ ተገልጿል።

በ35 ሄክታር መሬት ላይ ከቻይናው "ሲሲሲሲ" ጋር በመተባበር የሚገነባው ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በከተማ ውስጥ አዲስ ከተማን የመገንባት ያህል ግዙፍ ፕሮጀክት መሆኑንም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል፡፡

የኢኮኖሚ ዞኑ በውስጡ ትላልቅ ሞሎችን፣ የመኖሪያ አፓርትመንቶችን፣ ቢሮዎችን፣ የትምህርት እና የጤና ተቋማትን እንዲሁም ሰፋፊ መዝናኛዎችንና የውሃ አካላትን እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከላትን ያካተተ መሆኑንም ጠቁመዋል።

አዲሱ የኢኮኖሚ ዞን ለመዲናዋ አዲስ ገፅታ የሚያላብስ፣ ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነቷን የሚያጎላ፣ ተጨማሪ የውበት ምንጭ የሚሆን፣ ለነዋሪዎች ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እና ንግድን የሚያሳልጥ ትልቅ ዓለም አቀፍ የግብይት ማዕከል እንደሚሆን ከንቲባ አዳነች በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ ገልጸዋል፡፡

# ጠንካራ ቁጥጥርንና የማምረት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የማስከበር ተግባር ጥሩ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ዓይነቱ ርምጃ የአጭር ጊዜ መፍትሔ ሊሆን ይችላል እንጂ ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊሆን አይችልም፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ገበያው ላይ ጫና ያስከትላል የሚሉት ተመራማሪው፤ ገበያውን ከመቆጣጠር ባለፈ የመሠረታዊ ሸቀጦችን አቅርቦት የማሳደግ ሥራ መሠራት እንዳለበት ይገልጻሉ፡፡

ቀደም ሲል ተከታታይነት ያለውና መደበኛ የንግድ ሥርዓት ክትትል አለመኖሩን ጠቁመው፤ መንግሥት በተለያዩ አማራጮች ወደ ገበያው በመግባት ሸቀጦችን ለኅብረተሰቡ ማቅረብን ጨምሮ መሠረታዊ ሸቀጥ አቅራቢዎችን ማበረታታት እንደሚኖርበት ይናገራሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የሚመጣውን ጫና በዘላቂነት ለመቆጣጠር በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ማሳደግ እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ የመሠረታዊ ሸቀጦችን አቅርቦት በማሳደግ ገበያውን የማረጋጋት ሥራ መሠራት እንዳለበትም ይገልጻሉ፡፡

ማሻሻያውን ተከትሎ የሚመጡ ጫናዎችን ለመቆጣጠር መንግሥት እወስዳለሁ ያላቸውን እቅዶች ተግባራዊ መደረግ አለባቸው ሲሉም ያሳስባሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አድርገው ስኬታማ የሆኑ ሀገራት እንዳሉ በማንሳት፤ በተለይም የውጭ ንግዳቸው ተወዳዳሪ የሆኑ እንደ ጃፓን ያሉ ሀገራት ውጤታማ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ምርት ወደ ውጭ ከሚላከው በሚበልጥባት ኢትዮጵያም ይህን መሰል ማሻሻያ ማድረግ ጥንቃቄ እንደሚጠይቅ ገልጸው፤ የዋጋ ግሽበትን በማስከተልና፣ ሀብትን ወደ አላስፈላጊ በመዋል በኩል ጫና የሚመጣ በመሆኑ ኢኮኖሚው ላይ ጠንካራ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው አካል በሆነው የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሥርዓት ማሻሻያ ከመደረጉ በፊት በቂ የምግብና የመሰረታዊ ሸቀጦች ክምችት መኖር ነበረበት የሚሉት ደግሞ የምጣኔ ሀብትና ፋይናንስ ባለሙያው ኃይለመስቀል ጋዙ ናቸው፡፡

ማሻሻያው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት የዶላር ክምችቶች መኖር ነበረባቸው የሚሉት ባለሙያው፤ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሲደረግ ግሽበቶች ተጠባቂ መሆናቸውንና በአብዛኛው ከውጭ በሚመጡ ዕቃዎች ላይ የሚኖረው የዋጋ ንረት ቀላል የሚባል አለመሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የውጭ ምንዛሪው መጨመርን ተከትሎ ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚጣለው የታክስ መጠንም እንደሚጨምር ጠቁመዋል፡፡

የታክስ፣ የትራንስፖርት ወጪና ዶላር መጨመርን ተከትሎ ነጋዴው ከውጭ ያመጣው ዕቃ ላይ የዋጋ ጭማሪ እንደሚስተዋል ጠቅሰው፤ በሀገሪቱ ያለው የታክስ ህግ እንደገና መታየት እንዳለበትና የታክስ መጠኑንም ማሻሻያ እንደሚያስፈልገው ያብራራሉ፡፡

ከታክስ ነፃ የሚገቡ ሸቀጦች ላይ አግባብ ያልሆነ ጭማሪ በሚያደርጉ ነጋዴዎች ላይ ክትትል መደረግ ይኖርበታልም ይላሉ፡፡

የካርጎ፣ የባሕር ትራንስፖርት መጨመሩን ተከትሎ በካርጎ የሚመጣ ዕቃ በእጥፍ ጨምሯል የሚሉት ኃይለመስቀል፤ ከውጭ የሚመጡ መሠረታዊ ሸቀጦችን በተቻለ መጠን ሀገር ውስጥ በስፋት ማምረት ተገቢ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ይህን አቅም መፍጠር እስካልተቻለ ድረስ የዋጋ ጭማሪው የሚቆም እንዳልሆነ እና ጭማሪው የሚቀጥል መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ባንኮች አካባቢ ዶላር ሳይኖር አለ የሚባለው የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ መፈተሽ እንደሚያስፈልግ በመጠቆም፤ አስመጪዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕቃዎች በቂ ምንዛሪ አግኝተው ዕቃ ማስገባት ካልቻሉ የፍላጎት መጠን እየጨመረ ይሄድና ጫና እንደሚፈጥር ይገልጻሉ፡፡

ከእንዲህ ዓይነት ችግሮች ለመውጣት ሁሉም ባለድርሻ ተቋማት ማለት ባንኮች እና ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ከነጋዴዎች እኩል የሕግ ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

ባንኮች የያዙትን ዶላር ቢለቁ፣ ለውጭ ምንዛሪ አቅራቢዎች የተሰጠው ፈቃድ ተከትሎ በተወሰነ መልኩ ዕቃ የሚገባ በመሆኑ በገበያው ዋጋ ላይ መሻሻል ሊያመጣ እንደሚችልም ይጠቁማሉ፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን መንግሥት የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያን ተከትሎ ሊመጡ የሚችሉ ጫናዎችን ለመቋቋም ያስቀመጣቸው የድጎማ ሥርዓቶች የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ትልቅ አበርክቶ አላቸው ባይ ናቸው፡፡

ታክስ ከአጠቃላይ ሃገራዊ ምርት ያለውን ምጣኔን ማሻሻል፣ ምርታማነትን በማሳደግ፣ የወጪ ንግድ አቅምን ማጎልበት የሪፎርሙ ትኩረት መሆኑን የሚገልጹት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ ናቸው።

ማሻሻያውን ውጤታማ ለማድረግ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ የፀጥታ ሥራ መሥራትና የሎጀስቲክስ ሠንሠለትን ውጤታማ የማድረግ ጉዳዮች በትኩረት ይሠራል ነው ያሉት፡፡

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ወደ ዘመናዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት በተሟላ ሁኔታ በማሸጋገር፣ ተወዳዳሪነትን የሚያሻሽል፣ ምርታማነትን የሚያሳድግና የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር እንዲያስችል ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚደረግም ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም መንግሥት ነጋዴዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሕግ የማስከበር ሥራውን አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ምርታማነትን ማሳደግ፣ የቁጥጥር ሥራውን ማጠናከርና ከውጭ የሚገባውን ሸቀጥ በሀገር ውስጥ መተካት ሲቻልም የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው በኅብረተሰቡ ላይ ጫና ሳይፈጥር ስኬታማ ማድረግ የሚያስችል ይሆናል፡፡ ይህም ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ልማት እንደሚያመጣ ይጠበቃል፡፡

# የቴክኖሎጂ ፈጠራ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አካላት የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ካላት አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት 70 በመቶ የሚሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡ ወጣቶች የቴክኖሎጂን ዓለም በመቀላቀል ሥራ ፈጣሪ መሆንና የመፍትሔ ሀሳቦችን ማመንጨት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሀገሪቱ ከተረጅነት እና ከሥራ ጠባቂነት አስተሳሰብ ያልወጡ ወጣቶችም እንዳሉ ሁሉ በአካባቢያቸው የሚስተዋሉ ችግሮችን በቴክኖሎጂ ታግዘው የመፍትሔ ሀሳብ የሚሰጡና ሥራ የፈጠሩ ወጣቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም ወጣት አሸናፊ ወርቄ አንዱ ነው፡፡ የቀለም ሜዳ ቴክኖሎጂ መሥራች አባልና የሶፍት ዌር አበልጻጊ ነው፡፡ የተማሪዎች የፈተና ውጤቶችን ከእጅ ንክኪ በፀዳ መልኩ ማረም የሚያስችል ቴክኖሎጂ አበልፅጓል። ቴክኖሎጂው ክልላዊና ሀገራዊ ፈተናዎችን ማረምና መቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን ያስረዳል፡፡

ወጣቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ ቴክኖሎጂው የፈተና ውጤቶችን ከማረም በተጨማሪ ማን ከፍተኛ ውጤት አመጣ የሚለውን የሚለይ፣ ተማሪዎች ያለባቸውን ቅሬታ ያሉበት ቦታ ሆነው ማየት የሚችሉበት እና ሌሎች በርካታ ጥቅሞችን የሚያስገኝ ነው፡፡

የፈተና እርማት በሰው እጅ ሲሠራ ለስህተት ከመጋለጡም በተጨማሪ ረጅም ጊዜን ይወስዳል የሚለው ወጣት አሸናፊ፤ በዚህም የፈተና እርማትን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ተማሪዎች ትክክለኛ ውጤታቸውን ማግኘት የሚችሉበትን መፍትሔ እንደሚያቀርብ ይገልጻል፡፡


አሁን ላይ ቴክኖሎጂውን በሙከራ ደረጃ በ11 ክልሎች ያሉ የስድስተኛና የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ቤቶች እየተጠቀሙት ሲሆን፤ ኦሮሚያ ክልል በተጨማሪነት የሲ.ኦ.ሲ ፈተናን ለማረም እየተጠቀመበት እንደሆነም ገልጿል።

የቴክኖሎጂው ተጠቃሚዎች የማረም ሥርዓቱ በእጅጉ የዘመነና ተዓማኒነት ያለው መሆኑን ምስክርነት እየሰጡበት መሆኑን ገልጾ፤ ቴክኖሎጂውን ይበልጥ ለማስተዋወቅና በፌዴራል ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እንደሚያደርጉ ያስረዳል፡፡

ቴክኖሎጂው ከስህተት በፀዳ እና በአጭር ጊዜ ለማረም እንዲሁም ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ገልጾ፤ በአንድ ጊዜ የ900 ሺህ ተማሪዎች ፈተና ስካን ተደርጎ ገብቶ እርማቱ ሁለት ደቂቃ ብቻ ነው የሚወስደው ይላል፡፡ ይህም ጊዜን ለመቆጠብና



ወጣት አሸናፊ ወርቄ



ቢኒያም አስሙ (ዶ/ር)



ወጣት አቤል ማስረሻ

ከስህተት ነፃ ሆኖ ለመሥራት ሚናው ጉልህ እንደሆነ ያብራራል፡፡

ወጣት አቤል ማስረሻ ይባላል፡፡ በኤሌክትሪክ የሚሠራ እና ተጣጣፊ ዊልቸር ሠርቷል፡፡ በአፍሪካ ከ80 ሚሊዮን በላይ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ10 ሚሊዮን በላይ የእንቅስቃሴ ገደብ ያለባቸው የአካል ጉዳተኞች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዊልቸር ያላቸው ከአንድ በመቶ በታች በመሆናቸው ዊልቸሩን ለመሥራት እንዳነሳሳው ይናገራል፡፡

የሠራው ዊልቸር በሙከራ ደረጃ 30 ኪሎ ግራም ወይም የ10 ዓመት ልጅ የመያዝ አቅም ያለው ሲሆን፤ የዲዛይንና የወረቀት ሥራው ሲጠናቀቅ 120 ኪሎ ግራም ድረስ መያዝ ይችላል ይላል፡፡

የዊልቸሩን ባትሪ በመንቀል ቤት ውስጥ ባለ ማንኛውም ሶኬት ቻርጅ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፤ በአስፓልትና በኮብልስቶን መንገዶች እንደልብ መንቀሳቀስ ያስችላል። በማይመቹ መንገዶች ጭምር ምቾትን እንዳያሳጣ የሚያደርግ መሣሪያ እንደተገጠመለትም ያስረዳል፡፡

ሰው ማናገርና መጠበቅ ቢፈልግም ዜሮ ፍጥነት ላይ በማድረግ ባትሪውን እየቆጠበ መጠበቅ ይችላል፡፡ አንድ ጊዜ ባትሪው ተሞልቶ እስከ 30 ኪሎ ሜትር መሄድ ይችላል። አካል ጉዳተኛው ከ30 ኪሎ ሜትር በላይ የመሄድ አቅም ካለው ተጨምሮ መሥራት ይቻላል፡፡ ባትሪው የሚቀረውንና ስንት ኪሎ ሜትር እንደሚያስኬደው የሚያሳውቅ መሣሪያ ተገጥሞለታል ሲል ስለ ፈጠራ ሥራው ይናገራል፡፡

ለችግሮች መፍትሔ ማምጣት ስንችል ከራስ አልፎ ማኅበረሰብን መጥቀም የሚቻል በመሆኑ ወጣቱ የማኅበረሰብ ክፍል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለችግሮች መፍትሔ እንዲሰጡ መልዕክቱን ያስተላልፋል፡፡

ቢኒያም ዓለሙ (ዶ/ር) የብሉ ኸልዝ ኢትዮጵያ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ብሉ ኸልዝ ኢትዮጵያ ሠዎች የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምናን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ደራሽ የሚባል የሞባይል መተግበሪያ አብልፅጎ ለኅብረተሰቡ አበርክቷል፡፡

መተግበሪያው በድንገት በሚያጋጥሙ አደጋዎች ላይ መደረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን የሚያሳውቅ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በአቅራቢያ ያሉ የጤና ተቋማትንና የአደጋ ጊዜ ስልክ ቁጥሮችን በቀላሉ ማግኘት ያስችላል፡፡

በተጨማሪም ሰዎች የቅድመ ሕክምና እርዳታን በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ወጣቶች ሥራ ጠባቂ ሳንሆን ሥራ ፈጣሪ በመሆን ለሌሎችም ሥራ ፈጥረን በማሳየት ተሞክሮ መሆን አለብን ይላል፡፡

ሌላኛው የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለሙያ ወጣት ቢሊሱማ ጌታቸው ተማሪዎች በቀላሉ የሚማሩበት መተግበሪያን ማልማቱን ይናገራል፡፡ መተግበሪያው ተማሪዎች መጻሕፍት ላይ ያሉትን ስዕሎች በስልካቸው ስካን በሚያደርጉበት ጊዜ ገለጻና ማብራሪያ ያደርግላቸዋል ይላል፡፡

ቴክኖሎጂው አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችንም ተሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ ስካን በሚያደርጉበት ጊዜ በምልክት፣ በድምፅና በቪዲዮ ገለጻና ማብራሪያ ያደርግላቸዋል፡፡ ይህም የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ያስረዳል፡፡

በየካ አባዶና ሚያዝያ 23 ትምህርት ቤቶች በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን፤ በቴክኖሎጂው አምስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጥናት ሠርተውበት ውጤታማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

# ወቅታዊ

# " ደቡብ ሱዳን የናይል ስምምነት ማዕቀፍን ማጽደቋ የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲ ሥራ ውጤታማነት ማሳያ ነው"

**ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር)**
**የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር**

ሳሙኤል ወንድወሰን

**የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ቀደምት ከነበሩት ተቋማት መካከል የሚመደብ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 በአዲስ አደረጃጀት የተዋቀረ የፌዴራል መሥሪያ ቤት ነው።**

**ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ፣ በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ እና በኢነርጂ ልማት ዘርፍ የተዋቀረ ሲሆን የኢትዮጵያ ሜትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትና የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ደግሞ በተጠሪ ተቋምነት የተደራጁ ናቸው።**

**ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብት እድገት ወሳኝ የሆነውን የውሃና የኢነርጂ ሀብት ለይቶ በማልማት በማበልጸግና በማስተዳደር እንዲሁም የዜጎችን ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን ዘርፉ ለዜጎች ከሚያበረክተው ቀጥተኛ ጠቀሜታ ባሻገር ሌሎች ዘርፎች ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ መሻሻል ያስቀመጡትን ግብ ከማሳካት አኳያ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።**

**የዝግጅት ክፍላችን የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ምን ይመስላል? ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ተጠቅማለች ወይ? የውሃ ሀብቷን ለመጠቀም ምን ምን ሥራዎች ተሠሩ? እና የናይል ስምምነት ማዕቀፍ ለኢትዮጵያና ለተፋሰሱ ሀገራት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል።**

**አዲስ ዘመን፡- ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አጠቃቀም ምን ይመስላል? ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ተጠቅማለች ወይ?**

**ኢንጅነር ሀብታሙ ፡-** ባለፉት ዓመት ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት እያልን እንደ ሀገር ትልቅ አጀንዳ ተቀርጾ ይዘፈናል፣ ይጨፈራል፣ ይወራል። ይህ ለኛ ኩራት ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት በቂ ነው ወይ አይደለም? የሚለውን ካየን ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት እንዲሁም የልማት ፍላጎት አንፃር ኢትዮጵያ ተጨማሪ የውሃ ሀብት እንደሚያስፈልጋት ማሳያዎች አሉ።

ነገር ግን ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት መጠቀም ሳትችል ቆይታ እስከ አሁን በድህነት ውስጥ ትገኛለች። ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን አልተጠቀመችም የምንለው እንዲሁ ዝም ብለን ሳይሆን ምክንያቶች ስላሉን ነው።

በኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢዎች ሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ ኦሮሚያ፣ አማራ ክልል እና ሁሉም በሚባል ደረጃ በጣም ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችና ሊለሙ የሚችሉ ጠፍ መሬቶች ሳይለሙ ቁጭ ብለዋል። የሚለሙትም በዓመት ዝናብ ጠብቀው ነው።

ውሃዎቻችን ግን ከኢትዮጵያ ወጥተው ጎረቤት ሀገራትን ሲጠቅሙ እናያለን። በዛው ልክ ደግሞ ለረጅም ዓመታት ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ባለመቻሏ ስትወቀስ ነበር። ኢትዮጵያን የውሃ ሀብት በአግባቡ ስላልተጠቀመች ስትራብ ነበር። የሀገራችንን የውሃ ሀብት ባለመጠቀማችን መሬታችን ጾሙን ያድር ነበር።

ይህ የመጣው ካለመፈለግ ሳይሆን ከአቅም ማነስ ነው። አቅም ማነስ ሲባል የገንዘብ፣ የቴክኖሎጂ እና የመገንባት ሊሆን ይችላል። በነዚህ ጉዳዮች ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በአግባቡ ሳትጠቀም ቆይታለች።

**አዲስ ዘመን ፡- ከለውጡ በኋላ የኢትዮጵያን የውሃ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ምን ምን ሥራዎች ተሠሩ?**

**ኢንጅነር ሃብታሙ፡-** የኢትዮጵያ የልማት መሠረት መጀመር ያለበት ከውሃ ነው። ጠቅላይ ሚኒስቴሩም በሚሰጡት ከፍተኛ ትኩረት በውሃ ላይ የምንሠራቸውን



ሥራዎች እንዴት አድርገ በኢትዮጵያ ውስጥ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ውሃ መድረስ እንዳለበት የሚያሳዩ የተሳካ ሥራዎችን ሠርተናል።

**ኢትዮጵያ ቀድማ ማዕቀፉን ያጸደቀች ሲሆን ከዛ በኋላ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ ገብተውበት በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ የመጣውም በጋራ ለመልማት ካለ ፍላጎት አንፃር ነው**

ለአብነት በስንዴ ልማት የተገኘው አመርቂ ውጤት ዝናብ ብቻ ጠብቆ የመጣ ሳይሆን በዓመት ሶስት ጊዜ በማረስ ነው። ለዚህ ደግሞ መሠረቱ ውሃ ነው። በዚህም የውሃ ፓምፖችን በማቅረብና ትንንሽ የውሃ ማቆሪያ ቦታዎችን በማዘጋጀት በስንዴ ልማት አስደናቂ ውጤት ማምጣት ተችሏል። ይህም በቁጭት እየተሠራ ይገኛል።

የዓባይ ግድብን ብንመለከት ከ74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ መያዝ የሚችል ሐይቅ ለመፍጠር እየተሠራ ያለው ውሃን በአግባቡ ለመጠቀም ካለን ፍላጎት አንፃር የመጣ ነው። በፊትሃ ቢኖርም በዚህ ልክ በቁርጠኝነት የተሠራበት ጊዜ አልነበረም።

ስለዚህ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ውሃ ለኢትዮጵያ መሠረትና አስፈላጊ ነው ተብሎ በከፍተኛ ትኩረት በመንግሥት አቅጣጫ ተሰጥቶበት እየተሠራ ያለ ነው። የዓባይን ወንዝ ሳንጠቀምበት በመቆየታችን ቁጭት የፈጠረብን በመሆኑ በከፍተኛ ርብርብ እየተንቀሳቀስን እንገኛለን። ይህም ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

ከዚህ አልፎ ደግሞ እያንዳንዱ ኢትዮጵያው የንጹህ መጠጥ ውሃ በየአካባቢው እንዲያገኝ የሚደረገው ሥራ የውሃ ሀብታችንን በአግባቡ ለመጠቀም ያለንን ፍላጎት ያሳያል። ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት ያላትን የውሃ ሀብት በአግባቡ እንዳትጠቀም ተደርጋለች።

አሁን ግን ከዛ ተላቀን የውሃ ሀብታችንን ከመጠቀም አልፈን ወደ ውጤት መሻገር የጀመርንበት ደረጃ ላይ እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን ፡- የዓባይ ግድብ እና የኮይሻ ሃይል ማመንጫ የውሃ ሀብት አጠቃቀማችን ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ለመጀመራችን ማሳያ ናቸው ማለት ይቻላል? እንዴት?**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** አዎ የዓባይ ግድብ እና የኮይሻ ሃይል ማመንጫ የውሃ ሀብት አጠቃቀማችን ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ለመጀመራችን ማሳያ ናቸው። የዓባይ ወንዝ በየዓመቱ የኢትዮጵያን መሬት እየሸረሸረ፣ አደጋ እያደረሰ እና አገልግሎት ሳይሰጥ ሀገር አቋርጦ ይሄድ ነበር።

ከአሁን በኋላ እንደዚህ አይቀጥልም። ምክንያቱም ግድቡን በመገደባችን የፈለግነውን የውሃ መጠን ይዘን ቀሪውን መልቀቅ በኢትዮጵያውያን እጅ ሥር ያለ ነው። ኢትዮጵያ ከዓባይ ግድብ ጥቅም ልታገኝ ትችላለች። አንደኛው የኤሌክትሪክ ኃይል ሲሆን፣ ይሄም የዓባይ ግድቡ የሚሰጠውንና የሌሎች ግድቦችን ኃይል በመጨመር፣ የራሷን ፍጆታ አሟልታ፣ ከፍተኛ ኃይል ለሰሜንና ለምሥራቅ አፍሪካ በማቅረብ በውጭ ምንዛሪ የመሸጥ እድል ይሰጣታል።

ሌላው ግድቡ በሚፈጥረው ሐይቅ የሚዘጋጁት ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን በማስጠናት፣ እንደ የመስኖ እርሻ፣ የዓሣ ሀብት፣ የቱሪስት መዝናኛ፣ የውሃ ትራንስፖርት፣ የመጠጥ ውሃ ወዘተ የመሳሰሉትን በማልማት፣ ሀገሪቱን ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ያደርሷታል።

ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የግድቡ ግንባታ እስኪጠናቀቅ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በሌላ በኩል ኮይሻና ግልገል ጊቤ የኃይል ማመንጫ፣ መልካዋከና እና ፊንጫ የውሃ ሀብት አጠቃቀማችን ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ለመጀመራችን ማሳያዎቹ በእያንዳንዱ ቤት የምናየው የመብራት እና የውሃ አገልግሎት ተጠቃሽ ነው። በመስኖ ልማት የሚደረገው ርብርብም የውሃ ሀብት አጠቃቀማችን ማሳያ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሐምሌ ወር መጀመሪያ ደቡብ ሱዳን የናይል ስምምነት ማዕቀፍን ስድስተኛ ሀገር በመሆን በፓርላማ አጽድቃለች። ይህ ለተፋሰሱ ሀገራት ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? ኢትዮጵያ ማዕቀፉ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ የኢትዮጵያ ጥረት ምን ይመስላል?**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** በዓለም ላይ ወደ 276 የሚጠጉ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አሉ። ይህንን 145 የሚሆኑ ሀገራት ይጋራሉ። አንዳንድ ሀገራት ወንዞቹን የሚመለከት ሕግ አላቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የጋራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ የላቸውም። ነገር ግን ሕጉ ያላቸው ሀገራት ውሃን ዘላቂና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚነታቸውን እያረጋገጡ ይገኛሉ።

የናይል የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት የዓባይን ውሃ በጋራ፣ በእኩልነትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ውሃውን መጠቀምና አብሮ መንከባከብ የሚያካትትና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የሚተዳደሩባቸውን መርሆችን ጭምር ያካተተ ማዕቀፍ ነው። ይህም በአሥራ አንድ ሀገራት መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው።

ጉዳዩን የኢትዮጵያ መንግሥት የቅርብ ክትትል ያደረገበት በመሆኑ የተሳካ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተለያዩ ሀገራት መሪዎችን በሚያገኙበት አጋጣሚ የውሃ ሀብትን በጋራ ማልማትና መጠቀም የሚቻልባቸውን መንገዶች ያነሳሉ። ይህም የኢትዮጵያ የውሃ ዲፕሎማሲ ሥራ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ ቀድማ ማዕቀፉን ያጸደቀች ሲሆን ከዛ በኋላ ሩዋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ዩጋንዳ ገብተውበት በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል። ይህ የመጣውም በጋራ ለመልማት ካለ ፍላጎት አንፃር ነው። በቅርቡ ደግሞ ብሩንዲና ደቡብ ሱዳን በምክር ቤቶቻቸው አጽድቀውታል።

በየዓመቱ የናይል ተፋሰስ ኢኒሼቲቭ መድረክ ላይ የውሃ ሚኒስቴሮች ይሰበሰባሉ። በዚህም ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ሀገራት የውሃ ሀብቶችን በትብብር ማልማትና ማስተዳደር የሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ እና ለጋራ ተጠቃሚነት ሁሌም ቅድሚያ ትሰጣለች።

ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ መጠቀም ብቻ ሳይሆን የማልማትም ሥራ እያከናወነች ነው። ይህም በአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ በመትከል እየተሠራ ያለ ሥራ ነው።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ ደቡብ ሱዳን የናይል ስምምነት ማዕቀፍን ማጽደቋ...

ከገጽ 7 የዞረ

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለውሃ መጠን መጨመር ጉልህ ሚና አለው። ችግኞች በተተከሉ ቁጥር አካባቢ ላይ የሚደርሰውን የመሬት መራቆት ይቀንሳል። የደን ሽፋንን ያሻሽላል። የግድቦችንም እድሜ ያረዝማል ነው ያሉት።

ባለፉት አምሥት ዓመታት ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ በተከለቻቸው ከ32 ቢሊዮን በላይ ችግኞች ውስጥ ወደ ስምንት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን የሚሆነው የተተከለው በዓባይ ተፋሰስ ነው። የዓባይን ውሃ በማልማት የሚመጣው ጠቀሜታ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለታችኛው ተፋሰስ ሀገሮችም ጭምር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚሠራው የሳኒቴሽን ሥራ አንፃር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ የተደረገው የ “ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና” ንቅናቄ ምን ፋይዳ አለው? ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱንስ እንዴት ያግዛል?**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አንዱና በትኩረት ከሚሠራቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ የውሃና የሳኒቴሽን ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ በሁለት ሥራ አስፈፃሚዎች የሚመራ ሲሆን የሳኒቴሽን ሥራ ከፍተኛ ተግዳሮት የነበረበት ሥራ ሲሆን ይህም ከተሞች ለሥራው የሚሰጡት ትኩረት አናሳ በመሆኑ የተፈጠረ ነው።

የከተሞችን ንጽህናን ለመጠበቅ ከዓለም ባንክ ብር ተበድረን ጥናት ተሰርቶ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ ከተሞች ቦታ ለመስጠት ከማስቸገርም በላይ ሥራው እንዲሠራም አይፈልጉም ነበር።

ሚኒስቴሩ የከተሞች ውበትና ጽዳት እንዲጨምር እንዲሁም ሰዎች ጤናቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ ከፍተኛ ገንዘብ አዘጋጅቶ ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ነገር ግን ከተማን በሚያስተዳድረው አመራር የማይሆን ቦታ መስጠት፣ የሰጡትን ቦታ መውሰድ እና ሌሎች መሰል ችግሮች ሲያጋጥመው ቆይቷል።

ይህ ችግር በሳኒቴሽ ሥራ የነበረንን አፈፃጸም ዝቅ አድርጎታል። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ኢትዮጵያ እስከ አሁን በሳኒቴሽን ሥራ አመርቂ ውጤት አላስመዘገበችም። የተሠራው ሥራም ከ30 በመቶ አይበልጥም። ከተማን ከተማ የሚያስብለው ውብ፣ ንጹህ እና ለነዋሪዎች ምቹ ሲሆን ነው። ለዚህም የሳኒቴሽን ሥራ ጉልህ ሚና አለው።

ዘንድሮ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ የተደረገው የ “ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና” ንቅናቄ ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ለጤና ሚኒስቴር ከፍተኛ ድጋፍ እየሆነ ነው። ይህም ከዚህ በፊት በከተሞች የነበረውን ያለመተባበር ችግር እየፈታ ነው።

ንቅናቄው ከተሞች ለሳኒቴሽን ሥራ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ አድርጓል። ይህም ማለት የ “ጽዱ ጎዳና - ኑሮ በጤና” ንቅናቄ ለሳኒቴሽን እና ለአካባቢ ጽዳት በጎ ተጽዕኖ ከማሳደሩ በላይ በግንባር ቀደምነት ልዩ ድጋፍ እያደረገ የሚገኝ ንቅናቄ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በ2016 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሠሩ ዋና ዋና ሥራዎች ምን ምን ናቸው?**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** በውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ የተተገበረ ብሔራዊ የውሃ ጥራት ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ሽፋን ከነበረበት 24 በመቶ ወደ 33 በመቶ ማሳደግ ተችሏል። የገፀ ምድር ውሃ ሀብት አለኝታ ጥናት ሽፋን ከነበረበት 81 ነጥብ ሰባት በመቶ ወደ 83 ነጥብ ስድስት በመቶ ማሳደግ ተችሏል።

የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት አለኝታ ጥናት ሽፋን ከነበረበት 20 ነጥብ ሰባት በመቶ ወደ 24 ነጥብ ሰባት በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ ሶስት ነጥብ አንድ በመቶ በማከናወን አጠቃላይ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት አለኝታ ጥናቱን ወደ 23 ነጥብ ስምንት በመቶ እንዲያድግ ተደርጓል።

በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 70 ሚሊዮን 578 ሺህ 526 ወደ 76 ሚሊዮን 698 ሺህ 526 ለማሳደግ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ አራት ሚሊዮን 082 ሺህ 511 የህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ የተጠቃሚ ቁጥር ወደ 74 ሚሊዮን 661 ሺህ 037 ማሳደግ ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ አንድ ሚሊዮን 564 ሺህ 380 ነዋሪዎች (798 ሺህ 768 ሴቶች) በአዲስ አበባ፣ በክልል ከተሞች እና በገጠር መንደሮች ያሉ ነዋሪዎች የንፁህና የዘመናዊ የሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ፋሲሊቲ ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ አጠቃላይ 27 ሚሊዮን 218 ሺህ 903 ነዋሪዎች በመኖሪያ ቤቶቻቸው፣ በሥራ ቦታቸውና ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ የዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶችና ተያያዥ የሳኒቴሽን ፋሲሊቲዎች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።



በኢነርጂ ልማት ዘርፍ ከብሄራዊ ግሪድ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ከነበረበት አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ወደ አምሥት ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ 427 ሺህ 830 ደንበኞች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ ከግሪድ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ወደ አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል።

ከብሄራዊ ግሪድ ውጪ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ከነበረበት ሶስት ነጥብ አራት ሺህ ወደ ስድስት ሺህ ለማድረስ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ተጨማሪ 592 ደንበኞችን ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሺህ ደንበኞች የኦፍ ግሪድ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ ከኤሌክትሪክ ሃይል ሽያጭ የተገኘ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማሳደግ 163 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 140 ሚሊዮን ዶላር (ማለትም የእቅዱን ስምንት ነጥብ አምሥት በመቶ) ገቢ ተገኝቷል።

የንጹህ ኢነርጂ ቆጣቢ ማብሰያ ምድጃ ተጠቃሚ ደንበኞችን ከነበረበት 19 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ወደ 22 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ከአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ደንበኞችን ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ የንጹህ ኢነርጂ ቆጣቢ ማብሰያ ምድጃ ተጠቃሚ ደንበኞችን ቁጥር ወደ 20 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል።

የባዮጋዝ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ደንበኛ ቁጥር ከነበረበት 42 ነጥብ ስድስት ሺህ ወደ 49 ሺህ ለማሳደግ ታቅዶ ሶስት ሺህ 946 ደንበኞችን ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ የባዮጋዝ ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥር ወደ 46 ነጥብ አምሥት ሺህ ማሳደግ ተችሏል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2017 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሲሠሩ የታቀዱ ዋና ዋና ሥራዎችን ቢያብራሩልን?**

**በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ የሀገራችንን ጥቅምና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ በማስጠበቅ በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ የውሃ ሀብታችን ላይ ፍትሃዊ አጠቃቀምን የማረጋገጥ ተግባራት ይከናወናሉ፡**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** በውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ በዋናነት በሀገሪቱ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት እንዲሰፍን የማድረግ ሥራ የሚሠራ ሲሆን ለዚህም የተፋሰስና የውሃ አካላትን ደህንነት በመጠበቅ የውሃ ሀብት ግኝቱን አስተማማኝ የማድረግ ሥራ ይሠራል።

የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት በብዛትና በጥራት የመለየት፣ ውሃን ማዕከል ያደረገ በየተፋሰሶቹ ያለውን የውሃ ሀብት ለማልማት የውሃ ሀብት መረጃ ሥርዓት የማደራጀት እና የውሃ አካላት የተፈጥሮ ፍሰት መዛባት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎች ቅድመ መከላከል ተግባራት ይከናወናሉ።

በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ የሀገራችንን ጥቅምና ፍላጎት ሙሉ በሙሉ በማስጠበቅ በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ የውሃ ሀብታችን ላይ ፍትሃዊ አጠቃቀምን የማረጋገጥ ተግባራት ይከናወናሉ።

በተለይ ከሃይድሮ ፓወር እና ከመስኖ ልማት ጋር የሚገናኙ ፕሮጀክቶች ከተጋሪ ሀገራት በሚነሱ ጥያቄዎች እንቅፋት እንዳይጋጥማቸው የውሃውን አጠቃቀም በተመለከተ ከውሃው ተጋሪ ሀገሮች ጋር በትብብርና ፍታሃዊ ተጠቃሚነት መርህ መሠረት ጥቅማችንን የማስጠበቅ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍም በዋናነት የመጠጥ ውሃና የሳኒቴሽን ተደራሽነትን በማሳደግ ሀገራዊ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥራትና ፍትሃዊ ተደራሽነት በማረጋገጥ የዜጎችን ኑሮ የማሻሻል ሥራ የሚከናወን ሲሆን በዚህም በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 74 ሚሊዮን 661 ሺህ 037 ወደ 80 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

በዚህም ከአምስት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ይሆናሉ። አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ የገጠር ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 54 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ወደ 64 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ የከተማ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 19 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ወደ 20 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል።

ሌላው የኢትዮጵያን የውሃ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ማደራጀት ሥራ ነው። በዚህም በውሃ አካላት ላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚተከል ሲሆን የመረጃ ቴክኖሎጂው አጠቃላይ የውሃ ሀብትን ለማስተዳደር፣ የሀብቱን መገኛ አካባቢዎች በመለየት ለማልማትና የአጠቃቀም ስልቶችን የሚያመላክት ነው።

ይህም በ2017 በጀት ዓመት በትኩረት የሚሠራ ሥራ ነው። የኢትዮጵያን የውሃ ሀብት በምርምር የተደገፈና በተጨባጭ መረጃ የተደራጀ በማድረግ ዘላቂ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ይሠራል።

በተመሳሳይ በኢነርጂ ልማት ዘርፍ ደግሞ በዋናነት የዜጎችን የኢነርጂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚሠራ ሲሆን ለዚህም የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረትን ለማስወገድና ዘመናዊ የኢነርጂ ተደራሽነትን ለማስፋት ከውሃ ኃይል፣ ከንፋስ ኃይል እና ከሌሎች አማራጭ የታዳሽ ኃይል የኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ላይ ትኩረት ይደረጋል። በዚህም በርካታ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል።

በተጠሪ ተቋማትም በርካታ ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን ለአብነት በኢትዮጵያ ሜትዮሮሎጂካል ኢንስቲትዩት የሀገሪቱን የአየር ትንበያ በማከናወን የሚከናወኑ የልማት ተግባራት ከአየር ንብረቱ ጋር እንዲጣጣሙ የማድረግና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚከሰቱ አደጋዎችን መከላከል እንዲቻል ይደረጋል። ለዚህም ወቅታዊ የሆነ የአየር ጠባይ መረጃን ማጠናቀር፣ መተንበይና ማሰራጨት፣ የትንበያ መሣሪያዎቹ ዘመናዊና ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የሚሰጡ ትንበያዎችን ከዓለምአቀፍ ትንበያዎች ጋር የማጣጣም ሥራ ይሠራል።

በውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በውሃ ልማት ዘርፍ ለተሰማሩት መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፣ ወጪ ቆጣቢና ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማላማድና በማሸጋገር የማህብረሰቡ ተጠቃሚነትን የማሳደግ ሥራ ይሠራል።

**አዲስ ዘመን፡- እንግዳችን ስለሆኑ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ኢንጅነር ሀብታሙ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለሀብቶችን ተስፋ ያለመለመው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ

ማህሌት አብዱል

ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታና ስነምህዳር ካላቸው እና ተመራጭ ከሆኑ የዓለም ሀገራት አንዷ ነች። በተለይም የአየር ንብረቷ፣ ስነምህዳሯና ሰፊ የሰው ሀብቷ በዘርፉ መዋእለ ንዋያቸውን ስራ ላይ ለማዋል ለሚሹ ባለሀብቶች ሳቢ እንደሚያደርጋት ይገለጻል።

ይህንን እምቅ አቅም በመጠቀም ረገድ ያላት ተሞክሮ ከሁለት አስርት ዓመታት የማይዘልና ለምጣኔ ሀብት እድገትም የሚገባውን ያህል አስተዋፅኦ አበርክቷል የሚባል አለመሆኑም እየተጠቆመ ነው። በሀገሪቱ የግብርና ኢንቨስትመንት የሚገባው ያህል ማደግ ላለመቻሉና ካለው እምቅ አቅም አኳያ የላቀ አስተዋፅኦ እንዳያበረክት አድርገዋል በሚል ከሚጠቀሱ ተግዳሮቶች መካከል የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ዋነኛዎቹ መሆናቸው በተደጋጋሚ ይጠቀሳል።

የዘርፉን ችግሮች ከመፍታት አኳያ መንግሥት የተለያዩ ተግባሮችን ሲያከናውን መቆየቱ ይታወሳል። ከእነዚህም መካከል ከሰሞኑ ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ስርነቀል በሚባል ደረጃ ለውጥ ያመጣል ተብሎ የሚጠበቀው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ዋነኛው ነው። ይህ ማሻሻያ በተለይ በኢንቨስትመንትና ንግድ ላይ ለተሰማሩ ተዋናዮች አዲስ ተስፋ የፈነጠቀ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች እየተናገሩ ናቸው። ማሻሻያው በኢኮኖሚው ላይ ለረጅም ጊዜ የቆዩ መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት እና ዘላቂ እድገት ለማስፈን እንደሚያስችልም ታምኖበታል።

ማሻሻያው በተለይ በግብርና ኢንቨስትመንት የተሰማሩና ምርቶቻቸውን ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚልኩ ባለሀብቶች የዘመናት ጥያቄና የሥራ ማነቆ የሆነባቸውን የውጭ ምንዛሬ ጥያቄ የሚመልስ እንደሆነም ይጠቀሳል። ለመሆኑ የኢኮኖሚ ማሻሻያው ለአምራች ኃይሉ ምን ይዞ መጣ? ማሻሻያውን ተከትሎ የሚመጡ ለውጦችን መቋቋም የሚያስችል ነበራዊ ሁኔታስ ምንድን ነው? የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች ለዚህ ምላሽ አላቸው።

አቶ ካሳሁን ስንታየሁ በኦሮሚያ ክልል ሆለታ የሚገኘውና በደቡብ አሜሪካውያን ባለሀብቶች የተመሰረተው አፍሪ ፍላወር ኩባንያ ሲስተም አድሚኒስተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅታቸው ላለፉት አስርት ዓመታት ከ40 አይነት በላይ አበቦችን በማምረት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያስገባል። በ74 ሄክታር ላይ ያረፈው ይኸው የአበባ ልማት፣ ከ650 ለሚልቁ ዜጎችም የሥራ እድል የፈጠረ ነው። በቀጣዮቹ ዓመታት ኢንቨስትመንቱን የማስፋፋትና የሠራተኞቹንም ቁጥር በእጥፍ ለማሳደግ አቅዶ እየሰራ ነው። መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚያደርገው ድጋፍ የሚበረታታ መሆኑን አቶ ካሳሁን ጠቅሰው፤ በተለይ ለአበባ ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች አቅርቦት፣ ጊዜውን የሚዋጁ ቴክኖሎጂዎችንና የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት ላይ በርካታ ችግሮች እንደሚስተዋሉ አመልክተዋል።

ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ላይ በቆየባቸው ዓመታት እነዚህን ችግሮች ተቋቁሞ ኢንቨስትመንቱን ለማስቀጠል ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው፣ በተለይ የድርጅታቸው ዋነኛ ምርት የሆነው 'ሶፊሊያ' የሚባለው አበባ ለመፍካት የሚያስፈልገውን ስኳር ለማግኘት ለረጅም ጊዜ መቸገሩ ለሥራው ማነቆ ሆኖበት መቆየቱን ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል ድርጅታቸው የአበባ ማሸጊያና ኬሚካሎችን ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንደሚያስመጣ ተናግረው፣ ለዚህም የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ፈታኝ ሁኔታ እንደሚያጋጥመው ያነሳሉ። «ማሸጊያ ካርቶንም ሆነ ኬሚካል ለማምጣት የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ነው የሚያጋጥመን፤ በዚህ ምክንያት እንደምንፈልገው መንቀሳቀስም ሆነ ምርቶቻችን ለመላክ ተግዳሮት ሆኖብን ቆይቷል» ሲሉ ይናገራሉ።



አቶ ካሳሁን ስንታየሁ




አቶ መኮንን ዛጋ



አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ

በአሁኑ ወቅት ድርጅታቸው ከመንግሥት አካላት ጋር ባደረገው የረጅም ጊዜ ውይይት የስኳር ጥያቄ ምላሽ ማግኘቱን ይገልጻሉ። በቅርቡ ሀገሪቱ ወደ ሙሉ ትግበራ ያስገባችው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በተለይ በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ለተሰማሩ አካላት ተስፋ የፈነጠቀ መሆኑን አቶ ካሳሁን አስታውቀዋል።

« መንግሥት ኢኮኖሚውን ለመታደግ እየወሰዳቸው የሚገኙት ቁርጠኛ ውሳኔዎች በተለይ ለኢንቨስትመንት ማበብ በር የሚከፍቱ ናቸው። በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በርካታ ባለሀብቶች ዘርፉን እንዲቀላቀሉ ያደርጋል፤ የገቡትም ልማታቸውን እንዲያስፋፉ ያነሳሳል» በማለት ያስረዳሉ።

«ከዚህ ቀደም የውጭ ምንዛሬ በብሔራዊ ባንክ ይያዝብን ነበር፤ በዚህ ምክንያት ግብዓቶችን እንደፈለግን ማስመጣት፤ ማምረትም ሆነ መላክ ፈተና ይሆንብን ነበር፤ አሁን መንግሥት ባለሀብቱ ዶላር በቀላሉ ከባንክ ሄዶ የሚያገኝበትን ሁኔታ በመፍጠሩ ኢንቨስትመንቱ የበለጠ እንዲያድግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል» በማለትም ያብራራሉ። ይህ ሲሆንም ደግሞ ምርት ልኮ የሚያገኘውን የውጭ ምንዛሬ ውጭ ሳያስቀር ወደ ሀገር እንዲገባ ማድረግ እንደሚያስችል አቶ ካሳሁን ይገልፃሉ። ኢንቨስትመንቱ ባደገ ቁጥር ደግሞ ሰፊ የሥራ እድል ይፈጥራል፤ በስሩ የሚሰሩትንም ዜጎች የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋል የሚል እምነት አላቸው።

የሉሲ እርሻ ልማት የኮሜርሻል ዘርፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ መኮንን ዛጋ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በሀገር ውስጥ ባለሀብት የተመሰረተው ድርጅታቸው ላለፉት 25 ዓመታት በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ሰፊ ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል። በተለይም አርባ ምንጭ፣ ኦሞ እና ገዋኔ አካባቢዎች ላይ ባሉት እርሻዎቹ የተቀናጁ የግብርና ስራዎችን ይሰራል፤ በዋናነት የተመሰከረለትንና ተፈጥሯዊ (ኦርጋኒክ) የፍራፍሬና አትክልት ምርቶችን እንዲሁም ጥጥ፣ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችንም በስፋት በማምረት ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት በመላክም ይታወቃል። «ድርጅታችን በዋናነት ሙዝ፣ የቅባትና ጥራጥሬ እህሎችን ለመካከለኛው ምሥራቅ፣ ለምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት እንዲሁም ታይዋን፣ ሞሪሽየስና ታንዛኒያ ደግሞ የጥጥ ምርት በመላክ ለሀገራችን በየዓመቱ ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ያስገባል» ያሉት አቶ መኮንን ፤ በአሁኑ ወቅት ለአንድ ሺ 200 ዜጎች ቋሚ እንዲሁም ከስምንት ሺ ለሚልቁ የአካባቢው ነዋሪዎች ጊዜያዊ የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ያስረዳሉ።

ድርጅቱ ጥሬ የግብርና ምርቶችን ከመላክ በዘለለ እሴት የተጨመረባቸው ምርቶችን ለመላክና የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን በእጥፍ ለማሳደግ እቅድ ይዞ እየሰራ መሆኑን ያመለክታሉ። ከእርሻው ጎን ለጎን አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪውን በመቀላቀል ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል የመፍጠር ራዕይም አለው ይላሉ።

ድርጅቱ ይህንን ሰፊ የልማት ስራውን ለማሳካት ግን የመንገድና የኃይል መሰረተ ልማት፣ የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦት ችግር እንደስጋት የሚያየው መሆኑን አቶ መኮንን አመልክተዋል። « በእርሻ ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ አካላት የመንገድና የኃይል መሰረተ ልማት እንደልብ አለመኖር ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል» የሚሉት አቶ መኮንን፤ የፋይናንስ አቅርቦቱም ውስንነት ያለበት መሆኑ ኢንቨስትመንቱ እንዳይስፋፋ አድርጎታል የሚል እምነት አላቸው። በዚህ ረገድ መንግሥት በቅርቡ የወሰደው እርምጃ በብዙዎቹ የዘርፉ ተዋናዮች ዘንድ ተስፋ ያጫረ ስለመሆኑም ይናገራሉ።

«የፋይናንስ እጥረት አምራቹን አንቆ በአንድ ቦታ የሚያስቀር አንገብጋቢ ችግር ነው፤ አሁን ላይ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ይህንን ችግር ይፈታልናል ብለን እንጠብቃለን፤ በተለይ እንደእኛ ላሉ የግብርና ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ባለሀብቶች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪና የተሻለ ዋጋ እንድናገኝ ያደርጋል» ይላሉ።

ድርጅቱ በማሻሻያው የፋይናንስ እጥረቱ ይፈታል የሚል እምነት እንዳለው ጠቅሰው፤ የተሻሉ የገበያ አማራጮችን ለማስፋት እንደሚረዳውም ነው ያስታወቁት። በዚህ ረገድ ድርጅታቸው ማሻሻያው የሚያመጣውን ምቹ እድል በምን መልኩ ሊጠቀም እንደሚገባው አስቀድሞ ለማየት ጥረት ማድረጉን ይናገራሉ። ማሻሻያው ዘርፉን መቀላቀል ለሚሹ ትልልቅ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች በር እንደሚከፍት ተናግረው፣ ድርጅታቸው በምን መልኩ ተወዳዳሪ መሆን እንደሚገባው የራሱን ጥናት ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ መሆኑንም ያብራራሉ። ሌሎች የዘርፉ ተዋናዮችም ማሻሻያው ለትልልቅ ኩባንያዎች በር እንደሚከፍት እየጠቆሙ መሆናቸውን ተናግረው፤ ከዚህ አንፃር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ሰፊ ስራ እንደሚጠበቅባቸው አቶ መኮንን አስታውቀዋል። በተለይ ምርታማነትንም ሆነ ጥራትን ማሻሻል ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ይገባል የሚል እምነት አላቸው። ለዚህ ደግሞ አምራች ኃይሉ ድርጅታዊ አቋሙን ማጠናከርና ከዓለም ገበያ ጋር ተወዳዳሪ መሆን የሚችል ድርጅት መፍጠር እንደሚጠበቅበት ያመለክታሉ።

«ሁላችንም የዘርፉ አንቀሳቃሾች መጀመሪያ ውስጣዊ አቅማችንን ማጠናከር ላይ ትኩረት ልናደርግ ይገባል፤ የምርት ጥራትን ማሻሻልና አማራጭ ገበያዎችን መፈለግ ስንችል ነው ተወዳዳሪ ሆነን የምንዘልቀው» ሲሉም መክረዋል።

የሆርቲካልቸር አምራቾች ማህበር ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቴድሮስ ዘውዴ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ምቹ ከሆኑ ጥቂት የዓለም ሀገራት መካከል የምትመደብ ብትሆንም፣ ከዚህ አንፃር ባለፉት ዓመታት ዘርፉ መጠነኛ የሚባል እድገት ከማስመዝገብ ባለፈ በውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ በሥራ ፈጠራ በሌሎችም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች አነስተኛ አስተዋፅኦ ነው እያደረገ የቆየው። ይህ የሆነውም በዋናነት በመሬት፣ በፋይናንስና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ባሉ ችግሮች ምክንያት ነው። በተለይም ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ጭምር ማቅረብ የሚያስችል አቅም ቢኖራትም ይህንን አቅም መጠቀም ላይ ውስንነት ይስተዋላል።

በኢትዮጵያ ካለው እምቅ አቅም አኳያ፤ በተለይም ሰፊና የሚለማ መሬት፣ ጥራት ያለው የገፀ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር ውሃ አላት። ለመካከለኛውና ለአውሮፓ ገበያም ቅርብ ናት፤ ይሁንና ያለውን ምቹ ሁኔታ መጠቀም ላይ ክፍተት ይስተዋላል ሲሉ ያብራራሉ። በዘርፉ የሚታየውን ችግር በመፍታት ረገድ መንግሥትም ሆነ ማህበራቸው ቅንጅት ፈጥረው ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውንም አቶ ቴድሮስ ጠቅሰዋል።

በዚህም መጠነ ሰፊ የሚባል እድገት ማስመዝገቡን ይናገራሉ። «ባለፉት ዓመታት መንግሥት ኢንቨስትመንቱን ለማሳደግ ወሳኝ የሚባሉ እርምጃዎችን ወስዷል፤ ከእነዚህም መካከል እንደቴሌኮም ያሉና በመንግሥት ቁጥጥር ስር የነበሩ ተቋማትን ነጻ /ሊብራላይዝድ/ በማድረጉ በርካታ የውጭ ኢንቨስትመንቶች እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል» ይላሉ። የሆርቲካልቸር ኢንዱስትሪ በተለይ በወጭ ንግድ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን ተናግረው፣ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ለመገናኘት የቴሌ ኮም መሰረተ ልማት መስፋፋት ወሳኝ በመሆኑ ውሳኔው ጠቃሚ መሆኑን ያስረዳሉ። በሌላ በኩል የነፃ ገበያ ቀጣና መፈቀዱ ሌላው ዘርፉ ዳግም እንዲያንሰራራ እንደሚያደርገው አቶ ቴድሮስ ያመለክታሉ።

በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የግብዓትና የፋይናንስ አቅርቦቱ ሙሉ ለሙሉ መፈታት ከቻለ ደግሞ የዘርፉ ተወናዮች በዓለም ገበያ ላይ የበለጠ ተፎካካሪ መሆን እንደሚችሉ ያስገነዝባሉ። « ማሻሻያው መደረጉ በራሱ ኢንቨስተሩ እንደልብ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርገው በመሆኑ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ እንዲያመጣ ያደርገዋል፤ ኢትዮጵያ ያላትን የሆርቲካልቸር አቅምም በአግባቡ ተጠቅማ ልማቷን እንድታፋጥን ያግዛታል የሚል እምነት አለኝ» ሲሉም ነው ያስታወቁት።

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ማብራሪያ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ዓለምአቀፍ ኩባንያዎች ካፒታል ይዘው የሚመጡ በመሆኑ ሁኔታ የሀገር ውስጡንም የግል ዘርፍ ያነቃቃል ተብሎ ይጠበቃል። ይህም በሆርቲካልቸርም ሆነ በሌላ ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ አካላት ተጨማሪ እድል ይዞ ይመጣል።

የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን በማሻሻል ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ አቅም ይፈጥርላቸዋል። ገበያም ይዘው የሚመጡ በመሆኑ የሀገር ውስጥ አምራቾች እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች በአግባቡ መጠቀም የሚያስችላቸውን አቅም ሊያጎለብቱ ይገባል። ዝግጁነታቸውን አሁን የዓለም ኢንቨስትመንት በሚመጥን መልኩ ማዳበር ይጠበቅባቸዋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ሞትን በገንዘብ መግዛት

**እስማኤል አረቦ**

በኢትዮጵያ የትራፊክ አደጋ የሰዎችን ሕይወት በመቅጠፍና ለአካል ጉዳት በመዳረግ ወደር የለውም። ኢትዮጵያ ጥቂት ተሽከርካሪ ካላቸውና ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ እና ሞት መጠን ከሚመዘገብባቸው ሀገራት ግንባር ቀደሟ ናት።

በኢትዮጵያ በየቀኑ በአማካይ 14 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ምክንያት ሕይወታቸውን እንደሚያጡ እና 31 ያህሉ ደግሞ ለከባድ የአካል ጉዳት እንደሚዳረጉ ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በተመሳሳይ መረጃ ደግሞ በየሁለት ሰዓቱ አንድ ሰው እንደሚሞት ጥናቶች ያሳያሉ። 85 በመቶ የሚሆነው የትራፊክ አደጋ የሚከሰትባቸው አካባቢዎች ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ክልል እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች የሚደርሱ አደጋዎች ሲሰሙ ሰውነትን ይሰቀጥጣሉ፤ ጆሮን ጭው ያደርጋሉ።

በእነዚህም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት በሚደርሱ ዘግናኝ አደጋዎች እንደ ሰው ልባችን ሲሰበር ኖሯል። ሆኖም ችግሩ ዛሬም አልተቀረፈም። ከጥቂት ጊዜያት በፊት የደረሱትን የትራፊክ አደጋዎች መለስ ብለን ስንመለከትም ሰው ሆኖ መፈጠርን ጭምር እንድንጠላ የሚያደርጉ ናቸው። የጉዳታቸው ጥግም ከግለሰብም አልፎ ሀገር ላይ ጥቁር ዐሻራ ጥሎ የሚያልፍ ነው። ከእነዚህ ዘግናኝ አደጋዎች ውስጥ ጥቂቶቹን እናስታውስ።

ቦታው ሽጎሌ አካባቢ ነው። ከጳውሎስ ሆስፒታል ወደ ሽጎሌ በሚወስደው መንገድ ዓለም ፀሐይ ድልድይ አካባቢ አንድ የከተማ አውቶብስ ለለቅሶ የተጣለ ድንኳን ጥሶ በመግባት ባደረሰው ጉዳት የሶስት ሰዎች ሕይወት እንዲያልፍ ምክንያት ሆኗል።

አደጋው የደረሰው ቅዳሜ መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ሲሆን፤ የ 3 ሰዎች ሕይወት ሲያልፍ ከ20 በላይ ሰዎች ላይም ከባድና ቀላል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በድንኳን ውስጥ ለባለቤቷ ለቅሶ የተቀመጠች ኀዘንተኛም በዚሁ አደጋ ወላጅ እናቷንም አጥታለች። ሕይወታቸውን ያጡትና ጉዳት የደረሰባቸውም ኀዘንተኛዋን ለማጽናናት በድንኳን ውስጥ የተቀመጡ መሆናቸው ተነግሯል።

ሌሎች አደጋዎችን እንመልከት ። እሁድ ሐምሌ 9/2015 ዓ.ም. ንጋት ላይ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ደገም ወረዳ ወረቢ ተብላ በምትጠራ ሥፍራ አንዲት እናት አራት ልጆቿን ጨምሮ 14 ሰዎች ሞተዋል። በአደጋው ወቅት የ14 ሰዎች ሕይወት መጥፋቱን ፖሊስ ሲያስታውቅ ሦስት ሰዎች ደግሞ ቆስለው ነበር።

ለዚህ የትራፊክ አደጋ ምክንያቱ ቁልቁለት ቦታ ላይ ከባድ የጭነት መኪና በሕዝብ ማመላለሽ ሚኒባስ ላይ ስለወጣበት መሆኑን ፖሊስ ያስረዳ ሲሆን አደጋውን ያደረሰው የጭነት ተሽከርካሪ ከአዲስ አበባ ወደ ባሕርዳር 500 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ጭኖ ሲጓዝ የነበረ ተሳቢ መኪና ነው። ፖሊስም "ቁልቁለት ላይ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ሲጓዝ ነበር" ብሏል።

ከባድ ተሽከርካሪው ቁልቁለት መንገድ ላይ ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ በኋላ፣ ሁለት መኪኖችን ገጭቶ በመጨረሻ የሕዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ መኪና ላይ ሙሉ በሙሉ ስለወጣበት በውስጡ የነበሩ ሰዎችን ለሞት ዳርጓል።

በአደጋው ሕይወታቸውን ካጡት 14 ሰዎች መካከል መምህርት አስመሬ ጎሶማ እና አራት ልጆቿ ይገኙበታል። መምህርቷ የ 18፣ 15፣ 8 እና የ 1 ዓመት ልጆቻቸውን ይዘው ከአዲስ አበባ ወደ ጎሃ ጽዮን ቤተሰብ ጥየቃ እየተጓዙ የነበረ ሲሆን፣ በአደጋው የእናት እና የሁሉም ልጆቻቸው ሕይወት አልፏል።

ሌላውን አደጋ ደግሞ እንመልከት። በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ሱሉልታ ወረዳ ባጋጠመ የትራፊክ አደጋ ልጃቸውን አስመርቀው ሲመለሱ የነበሩ አባት ከተመራቂ ልጃቸው ጋር ሕይወታቸው ያለበት አደጋ ሁልጊዜም የሚረሳ አይደለም። አቶ ደረጀ ጌታቸው የተባሉት አባት ከሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀችውን ረድኤት ጌታቸው የተባለችውን ልጃቸው ይዘው ወደ መኖሪያ ከተማቸው ሲመለሱ ነበር የትራፊክ አደጋው አጋጥሞ ሕይወታቸው ያለፈው።

የ51 ዓመቱ የደብረ ሊባኖስ ወረዳ ሠራተኛ የሆኑት አቶ ደረጀ ሁለተኛ ልጃቸውን አስከትለው በሴት ልጃቸው የምርቃት ሥነ-ሥርዓት ላይ ለመታደም ወደ ሃዋሳ ያቀኑት ሐምሌ 13/2015 ዓ.ም. ነበር። ከምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ በኋላ ቅዳሜ ሐምሌ 15/2015 ዓ.ም አባት እና ሁለት ልጆቻቸው ሰሜን ሸዋ ውስጥ ወደ ሚገኛው መኖሪያ ከተማቸው ሻራሮ እየተመለሱ ሳለ ነው ከአዲስ አበባ በስተሰሜን 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ሱሉልታ ውስጥ ነበር የትራፊክ አደጋው የደረሰው።

በአደጋው የአቶ ደረጀ እና የልጃቸው ረድኤት ደረጀ ሕይወት ወዲያው ሲያልፍ የ 16 ዓመቱ ታናሽ ልጃቸው ላይ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶበታል።

የአቶ ደረጀ የቅርብ ጓደኛ እና ጎረቤት የሆኑት አቶ አሸናፊ አብዲሳ ለቢቢሲ ሲናገሩ የረድኤት ምርቃትን በማስመልከት ድግስ ተደግሶ ወዳጅ ዘመድ ከቤት ሆኖ መምጣታቸው ሲጠበቅ ነው አደጋው መድረሱ የተሰማው። "ለምረቃው ከብት ታርዶ፣ ጠላ ተጠምቆ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። እኔም እንደ ጓደኛ እና ጎረቤት ተሳትፎ ሳደርግ ነበር። የረድኤት እናትም ተመርቃ የምትመጣዋን ልጃቸውን ለመቀበል እየጠበቁ ነበር። ጎረቤት በሙሉ ቤት ሲደርሱ ለመቀበል እየተጠባበቅን ነው ይህን መርዶ የሰማነው።"

የትራፊክ አደጋው የደረሰው ወደ መኖሪያ አካባቢያቸው ሊደርሱ 50 ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው፣ ሱሉልታ ወረዳ ቆሬ ሮባ ተብሎ በሚጠራ ሥፍራ ነው። ረድኤት ደረጀ ከሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ በኬሚካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቷን ተከታትላ ለምረቃ የበቃች ሲሆን፣ ወላጆቿ ከምርቃቷ በኋላ ሥራ ይዛ ትጦረናለች ብለው ተስፋ ሰንቀው እንደነበረ ቢቢሲ ያናገራቸው የሟች ጎረቤት እና ጓደኛ ገልጸዋል።

"ይህ አደጋ እጅግ ሰቅጣጭ ነው። ለቤተሰብ አይደለም፤ ለጎረቤት አይደለም አደጋውን ለሰማው ሁሉ በጣም ከባድ ነው። ልጃቸውን በደስታ አስመርቀው ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ልጅ እና አባት እንደወጡ ቀርተዋል" በማለት አቶ አሸናፊ የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን ለቢቢሲ አማርኛ ክፍል ገልጸዋል።

የሱሉልታ ወረዳው ኮሚዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት እንዳለው ለአባት እና ልጅ ህልፈት ምክንያት የሆነው የመኪና አደጋ የደረሰው ሲጓዙበት የነበረው ተሽከርካሪ ከሌላ መኪና ጋር ተጋጭቶ መሆኑን አመልክቷል። በዚህም ሳቢያ አባት እና ልጅን ጨምሮ አምስት ሰዎች ለህልፈት ተዳርገዋል።

እነዚህ ሁሉ አደጋዎች ዘግኛኝ ከመሆናቸውም በላይ የሰዎችን ሕይወት ቀጥፈዋል፤ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፤ ንብረት አውድመዋል፤ ቤተሰብ በትነዋል፤ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ኪሳራ አስከትለዋል፤ እንደሀገርም ዋጋ አስከፍለዋል።

ከ1.5 ሚሊዮን ብዙም ያልዘለለ ቅተኛ የተሽከርካሪ ቁጥር ላላት ሀገር ኢትዮጵያ የአደጋው መጠን ከፍተኛ እንዴት ሊሆን ቻለ የሚው የራሱ ሆነ ጥናት የሚያስፈልገው ቢሆንም በዋነኝነት ግን ችግሩ የተያያዘው ከአሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ ጋር የተያያዘ መሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። በሀገሪቱ ከሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች 68.3 በመቶ ያህሉ ምቹ በሆኑ መንገዶች ላይ የሚከሰቱ መሆናቸው እና ከሚደርሱት አደጋዎች መካከል 85.9 በመቶ በአሽከርካሪው ስህተት፣ 3.3 በመቶ በተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ጉድለት፣ 2.8 በመቶው ደግሞ በእግረኞች ችግር የሚያጋጥሙ ናቸው።

> **ያለ በቂ ልምድና ሥልጠና መንጃ ፈቃድ ማውጣት ማለት ሞትን በራስ እና በሌሎች ንጹሃን ላይ መጋበዝ መሆኑን የሚረዱ ጥቂቶች ናቸው። መንጃ ፈቃድ በገንዘብ ማውጣት ማለት ሞትን እቤት ድረስ መጋበዝ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል**

በመንገድ ችግር የሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች 0.7 በመቶ ብቻ መሆናቸውን የመንገድ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ጥናት ያመለክታል።

ስለዚህም አደጋውን በዘላቂነት ለመከላከል አሽከርካሪዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም የአሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ ለዚህ ሁሉ አደጋ መንስኤ እንደሆነ በጉዳዩ ዙርያ የሚሠሩ የትራፊክ ባለሙያዎችና የትራንስፖርት ዘርፍ ኤክስፐርቶች ይናገራሉ።

በተለይም አሁን አሁን መንጃ ፈቃድ የሚሰጥበት መንገድ በአብዛኛው ከገንዘብ ጋር የተያያዘ መሆኑ ለአደጋው መበራከት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን የሚናገሩ ብዙ ናቸው። በአግባቡ አስፈላጊውን ስልጠና ወስዶና ተምሮ መንጃ ፈቃድ የሚያወጣው ሰው ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱና በምትኩ እቤታቸው ቁጭ ብለው መንጃ ፈቃድ የሚመጣላቸው ሰዎች መብዛታቸው የአደጋውን ቁጥር ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን እንዳደረገው ይናገራሉ።

ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት በተሰበሰበ መረጃ አንድ ሰው መንጃ ፈቃድ ለማውጣት ወራትን መሠልጠንና መማር አይጠበቅበትም። 28ሺ ብር ካለው እቤቱ ድረስ መንጃ ፈቃድ እንደሚመጣለት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ሃሳባቸውን አጋርተውኛል።

ተመዝግበው ሥልጠናና ትምህርቱን ወሰዱ የሚባሉትም ቢሆኑ በስተመጨረሻ 4 ሺህ ብር ጉቦ መክፈል የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህንኑ በመተማመን በበቂ ሁኔታ ሥልጠናውን ከመውሰድ ይልቅ የሚከፍሉት 4ሺህ ብር በመተማመን ወደ ፈተና የሚሄዱና የመንጃ ፈቃድ ባለቤት የሚሆኑ በርካቶች ናቸው።

ያለ በቂ ልምድና ሥልጠና መንጃ ፈቃድ ማውጣት ማለት ሞትን በራስ እና በሌሎች ንጹሃን ላይ መጋበዝ መሆኑን የሚረዱ ጥቂቶች ናቸው። መንጃ ፈቃድ በገንዘብ ማውጣት ማለት ሞትን እቤት ድረስ መጋበዝ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ማሽከርከር ትልቅ ሙያ ከመሆኑም ባሻገር ከፍተኛ ኃላፊነትንም የሚጠይቅ ነው። ከራስም አልፎ የሌሎችን ሕይወት የሚቀጥፍና በርካቶችንም ለማይሽር ጠባሳ እና ጉዳት የሚዳርግ ነው። ሆኖም ብዙዎች አሽከርካሪነትን የሚመለከቱት መሪ መጨበጥንና በጎዳና ላይ ፈልሰስ ብሎ መሄድን ብቻ ነው። ጉዳዩ ግን ከዚህ በጣም የራቀ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የትኛውም ሙያ ቢሆን የዚህን ያህል አደጋ የሚያስከትል የለም። በሙስናና እና በብልሹ አሠራር ምክንያት በእንዝላልነትና በግዴለሽነት በሚታደሉ መንጃ ፍቃዶች የብዙዎችን ሕይወት አጨልመዋል፤ በርካቶችን እስከወዲያኛው እንዲያሸልቡ አድርጓቸዋል፤ ለማይሽር የአካል ጉዳት ዳርጓቸዋል።

ቤተሰብን በትኗል፤ እናትን ያለልጅ አስቀርቷል፤ ልጅን ወላጅ አልባ አድርጓል፤ የሚዋደዱ ባልና ሚስቶች እንደ ቀልድ ወጥተው በዛው ቀርተዋል፤ በአንድ ጀንበር አንድ ሙሉ ቤተሰብ ከመኖር ወደአለመኖር ተሸጋግሯል።

ይህ ሁሉ እየታየ ግን ዛሬም መንጃ ፈቃድ እንደቆሎ ይቸበቸባል። አንደዳቦ በየቤቱ ይታደላል። ይህ ጉዳይ የሚመለከተውም የትራንስፖርት ባለሥልጣን አደጋው አፍንጫው ሥር ሆኖ ሺዎችን እየፈጀ ዝምታን መርጧል።

# የዘመን ጥበብ

# ‹‹ሸሙኔ›› የቋንቋና ወግ ጨዋታ

ዋለልኝ አየለ

የመጽሐፉ ስም፡- ሸሙኔ

ደራሲ፡- መስፍን ወንድወሰን

የህትመት ዘመን፡- 2016 ዓ.ም

የገጽ ብዛት፡- 217

የመሸጫ ዋጋ፡- 496 ብር

መጀመሪያ መጽሐፉ በማህበራዊ ገጾች ላይ በአንዳንድ ሰዎች ሲዘዋወር ተመለከትኩ። መጽሐፍ ፌስቡክ ላይ ማስተዋወቅ የተለመደ ስለሆነ ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። እየቆየ ሲሄድ ግን ተደጋገመብኝ። ሰዎች የራሳቸውን አተያይ ጽፈው አየሁ። አብዛኞቹ ቋንቋው ላይ አተኩረዋል። በኋላ ግን የማህበረሰብ ቱባ ቋንቋና ወግ እንደምወድ የሚያውቅ አንድ ጓደኛዬ ይህን መጽሐፍ ማንብ አለብህ አለኝ። አነበብኩት።

ብዙዎች መጽሐፉን ሳላስቀምጥ ነው የጨረስኩት፣ በአንድ ቀን ነው የጨረስኩት፣ በአንድ ምሽት ነው የጨረስኩት... እያሉ ገልጸውታል። እኔ ግን በተቃራኒው ነው የሆነብኝ። ያቺ 215 ገጽ መጽሐፍ ሙሉ ቅዳሜና እሁድ፣ እንዲሁም አንድ ምሽት ወስዳብኛለች።

እያነበብኩ ሳለ በአንዲት ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ወደ ሀገር ቤት እሄዳለሁ። ሌባ ጣቴን ያለሁበት ገጽ መሃል ላይ አድርጌ መጽሐፉን አጥፌ በቁዘማ ሄጃለሁ። አንድ ዓረፍተ ነገር ባነበብኩ ቁጥር በአካባቢያዬ የማስታውሰው አንድ ሰውዬ ይመጣል። የረሳሁትን አካባቢ ያስታውሰኛል። አንድ ወግ ሌላ እኔ የማውቀው የአካባቢ ወግ ያመጣብኛል። መጽሐፉን ሳነብ፣ ካነበብኩት ይልቅ የጻፍኩት ሳይበልጥ አይቀርም። እየቆሰቆሰ የሚያስታውሰኝን የስነ ቃል ግጥሞች ጻፍ ጻፍ ይለኛል። መሳጭ ብቻ ሳይሆን ቆስቋሽ መጽሐፍ ነው።

የስነ ጽሑፍ ባለሙያ ስላልሆንኩ ከስነ ጽሑፋዊ ቅርጽና ዘውግ አንፃር ምንም ማለት አልችልም። አንድ ነገር ግን ያጓጓኛል። የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች በዚህ መጽሐፍ ላይ ሒስ ሰርተውበት ማየት! ‹‹ምን ይሉ ይሆን?›› እላለሁ። ምክንያቱም በየመድረኩ ሲናገሩ እንደሰማኋቸው፣ በመጽሔት ሲከራከሩ እንዳነበብኩት፤ ኪነ ጥበብ ተፈጥሯዊ ስሜትን በነፃነት መግለጽን ይጠይቃል። ስነ ጽሑፍ ያዩትን፣ የሰሙትን እና በውስጥ የተፈጠረን ስሜት መግለጽ ነው። እዚህ ላይ እንግዲህ ‹‹ስታንዳርዳይዜሽን›› እና ‹‹ፖፕላራይዜሽን›› የሚሉት አላቸው።


‹‹ስታንዳርዳይዜሽን›› ማለት አንባቢን ታሳቢ አድርጎ መጻፍ ማለት ነው። የጽሑፉን መልዕክት ታሳቢ በማድረግ ለሆነ ዓላማ የሚጻፍ ማለት ነው። በአጭሩ ለማስተማር ማለት ነው። ይህ ብዙ ጊዜ ለጋዜጣና መጽሔት ሲሆን በዚህ አይነት መንገድ የሚጻፉ መጻሕፍትም አሉ።

‹‹ፖፕላራይዜሽን›› ማለት ግን በቀጥታ የተፈጠረውን ስሜት መጻፍ ማለት ነው። ያዩትንና የሰሙትን መጻፍ ማለት ነው። ዋና ዓላማው ስሜትን መግለጽ ነው። ስነ ጽሑፍ በዚህኛው መንገድ ሲጻፍ ነው ጥሩ ተብሎ ይታመናል፤ ወዲህ ደግሞ ማህበረሰብን ማስተማር አለበት የሚል ክርክር አለ። ሰፊ ማብራሪያውን ለስነ ጽሑፍ ባለሙያዎች እንተወውና ሸሙኔ መጽሐፍን እንመልከት።

የመጽሐፉ መቼት አማራ ሳይንት ውስጥ ነው። በይዘት በኩል፤ ዋና ገጸ ባህሪው አዝማሪ ሲሆን ከቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት እስከ ኢህአዴግ ድረስ ያሉትን ዘመናት ይመላለስባቸዋል። በተለይም በ1977 ዓ.ም የተከሰተውን ረሃብ የሚገልጽበት መንገድ ያስለቅሳል። ወዲህ ደግሞ ወግና ጨዋታው እንደገና ያስቃል። እያሳቀ እያስለቀሰ ያልኖርንበትን ዘመን ጭምር ያሳየናል።

በስነ ጽሑፍ ደረጃ ደግሞ በቋንቋ ይጫወታል። የስነ ጽሑፍ ውበቱ ቋንቋ ነው ይላሉ ባለቤቶቹ። ቋንቋ ሲባል ታዲያ አንድ ወጥ የሆነ የጋራ አገላለጽ አይደለም፤ የየራሱ ቀለም ያለው የፀሐፊዎች አገላለጽ ማለት ነው።

እዚህ ላይ ደራሲው አንድ ልዩ ነገር አሳይቶናል። ብዙዎቻችን ኖርንበት፣ አደግንበት፣ ስንናገራቸው የነበርናቸውን ቃላት ረስተናቸዋል። የምናነባቸው መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች፣ የምንከታተላቸው መድረኮችና መገናኛ ብዙኃን፣ አዋዋላችንና በዙሪያችን




ባሉ ሰዎች ተፅዕኖ ሌላ የቋንቋ ባህል አዳብረናል። ደራሲው በዚህ ሁሉ የትምህርትና የሥራ ሂደት ውስጥ ሲያልፍ (የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህር እንደነበር ሰምቻለሁ) ያንን ቱባ ባህልና ቋንቋ አልዘነጋውም።

ሰው እንዴት በዚያ ልክ በጥንቃቄ ራሳቸው የተናገሩት እስከሚመስል ድረስ በገጠር ሰዎች ዘዬ ይጽፋል? ወይስ ራሱም ሲናገር በእነዚያ ቃላት ይሆን? (ሲናገር ስላልሰማሁት)፤ ወይስ በቦታው ላይ በቆየባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሚናገሩትን እየቀረጸ ነበር? ግራ ቢገባኝ ምናልባት ድምጻቸውን እያዳመጠ ይሆን የጻፈው? የሚል ስሜት ፈጥሮብኛል።

እኔ እልም ያለ ገጠር ውስጥ ነው ያደግኩት። ምንም እንኳን ዘዬ ከአካባቢ አካባቢ የሚለያይ ቢሆንም መጽሐፉ እኔ ባደኩበት አካባቢ የሚነገሩ ብዙ ዘዬዎች አሉበት። ዳሩ ግን እነዚያን ቃላት ከመርሳቴ የተነሳ ሰምቼው የማላውቀው ቃል እየመሰለኝ ‹‹ምን ማለት ይሆን?›› እያልኩ በጽሑፉ ዓውድ ለመረዳት እታገላለሁ። ደግነቱ ጭራሹንም የማላውቃቸውን ቃላት ሳይቀር በዓውዱ መረዳት በጣም ቀላል ነው። እንደ መዝገበ ቃላትም ጭምር ያገለግላል ማለት ነው፡ መስማት ብቻ ሳይሆን ስናገራቸው የነበሩትን ቃላት ግን እኔ ረስቻቸዋለሁ። በኋላ ትዝ ሲለኝ ለካ ያ ቃል እኔ በጽሑፍ ቋንቋ ተላምጄው እንጂ የሚታወቅ ነበር። እንዲህ እያደረገ በቋንቋ ይጫወታል፤ ያጫውታል።

መጽሐፉ የማህበረሰብ ጥናት (ሶሾሎጂ) ለሚያጠኑ ሰዎች ብዙ ነገር ይነግራል። በነገራችን ላይ የማህበረሰብን ምንነት ለማወቅ ቃለ መጠይቅ ከማድረግ ወይም መጠይቅ ሰጥቶ ከማስሞላት ይልቅ እንደ ሸሙኔ አይነት መጽሐፍ ማንበብ ይበልጣል። ቃለ መጠይቅ በምናደርግበት ጊዜ የሚነግሩን በዚያ ቅጽበት የሚኖራቸውን ስሜት ነው። በሌላ በኩል ውስጣቸው ነፃ አይሆንም። የሆነን ነገር ታሳቢ አድርገው የሚፈሩት ነገር ይኖራል፤ የሆነ ነገር ያሳጣናል ወይም ያስገኝልናል ከሚል የውስጥ ትግል ጋር ነው የሚናገሩት። ምን ብናገር ይፈለጋል? ጠያቂው ምን ፈልጎ ይሆን? ምን ለማድረግ ይሆን? የሚል ነገር በውስጣቸው ይመሳሰላል። ስለዚህ በነፃ ልቦና አናገኛቸውም።

ስነ ቃል እና ሌሎች ወጎቻቸው ግን ሰው አዝዟቸው ሳይሆን የውስጥ ስሜት አዝዟቸው፣ ነፍሳቸው የሚመራቸውን የሚናገሩት ነው። ስለዚህ ትክክለኛ የማህበረሰብ ምንነት የሚገኘው ከእንዲህ አይነት ቱባ ባህልና ወግ ነው።

ሸሙኔ የሚነግረን ይህን የማህበረሰብ ፍልስፍና እና ወግና ልማድ ነው። ድንገት ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ። የማለቅሰው በገጸ ባህሪው በተገለጸው ታሪክ ውስጥ በአካባቢያችን ወይም በቤተሰብ የማውቀው እውነተኛ ታሪክ ስላለ ነው። ለምሳሌ፤ ምሽኞት (የአዝማሪው ሚስት) ከሞተች በኋላ ልጆቿ ልብሷን እያወጡ ያሸቱታል። በአካባቢያችን እናት ወይም አባት እህት ወይም ወንድም፣ ልጅ ወይም ሌላ የቅርብ ቤተሰብ ሲሞት ልብስ ይዞ ማልቀስ የተለመደ ነው። ለሚመለከቱ ሰዎች በጣም የሚረብሸው ግን ሟች ከሞተ ከብዙ ጊዜ በኋላ ልብሱን እያወጡ ማሽተት ነው። ይህ የማውቀው ልማድ ስለሆነ እንዲህ አይነት ልማዶችን እየጠቀሰና እያስታወሰ ያስለቅሰኛል።

በገጠር ውስጥ ያለው ማህበረሰብ ፍልስፍና አልተነገረለትም። የኪነ ጥበብ፣ የሳይንስ፣ የእምነት፣ የፍልስፍና ምንጩ ከዚያ ሆኖ፣ ዳሩ ግን አልተነገረለትም። ዘመናዊ በሚባለው ተውጧል። ፍልስፍናቸው ግን ጥልቅ ነው። እንዲያውም መጽሐፉ አንዳንድ ጊዜ ከስነ ጽሑፍ ይልቅ ሪፖርት ይሆንብኛል። እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ታሳቢ ይደረግ። የጋዜጠኝነት ሙያ በባህሪው ከቋንቋ ውበት ይልቅ ገለጻ (ይዘት) ላይ ስለሚያተኩር የዚያ ተፅዕኖ ስለሚኖርብኝ ይሆናል።

የገጠር ሰዎች በጣም ሲበዛ አማኝ ናቸው አይደል? ይህንን ማንም ያውቃል። የሚገርመው ግን በፈጣሪ ላይ ሳይቀር ያምጻሉ፤ ፈጣሪን ይቆጣሉ። በነፃነት ይፈላሰፋሉ። ሸሙኔ ይህን ሁሉ ነው የሚነግረን። ለምሳሌ፤ በመጽሐፉ ገጽ 14 ላይ የሚከተለውን እናገኛለን።

‹‹እግዜርን አኩርፈህ ነበር የሚባለው እውነት ነው?››

‹‹እንዴታ!››

‹‹ከቶ ምን ቢያደርግህ ከኸለቀህ ተጣላህ?››

‹‹የኸለቀ አካላቴን በሞላ በእሳት ጎረብ ቢመታኝ››

‹‹አዲያ አሁን ጠብ ነህ እርቅ?››

‹‹እርቅ። ተርቅም ሽርክ!››

............ እያለ ይቀጥላል። የገጠር ሰዎች ወግና ጨዋታ ሲያደምቁ በፈጣሪ ላይ ሳይቀር በመቀለድ ነው። ለምሳሌ፤ በክረምት ዝናብ ሳይዘንብ ዋል እደር ካለ ‹‹አንተዬ ይሄ እግዜሃር ክረምት መሆኑን ረሳው እንዴ?›› ብሎ ይጠይቃል አንዱ ገበሬ። ‹‹ምን አንተ ዴሞ እንዴት አይረሳው! አረጀ እኮ!›› እያለ ይመልሳል ሌላኛው። በዚህ ልክ ቀለል ብሏቸው መቃለዳቸው ያስፈራኝ ነበር።

ሸሙኔ መጽሐፍ እንዲህ የረሳናቸውን ወጎች ያስታውሳል። የማህበረሰብን ቱባ ምንነት ይነግረናል።

መጽሐፉ ምናልባት ለከተማ አደግ ሰዎች ግን የሚያስቸግር ይመስለኛል። ቀደም ሲል እንዳልኩት የቃላቱን ትርጉም ለማወቅ ዓውዱ ስለሚነግረን አያስቸግርም። አንዳንድ ቦታ ግን ሙሉ ዓረፍተ ነገሩ አዲስ ሊሆንባቸው ይችላል ብዬ የምፈራው አለ። በእርግጥ የስነ ጽሑፍ ውበቱም ይሄው ነው። የሆነ ነገር ፍለጋ አዕምሮን ማሰራት።

ሸሙኔ የንግግር ቃላትን ስለሚጠቀም አንዳንድ ሰዎች ያስቸግራቸው ይሆን? እያልኩ እፈራለሁ። ወይም ደግሞ ‹‹ይሄን ካላወቁት ቀረባቸው!›› እያልኩ እቆጫለሁ። እኔ ሳነበው ዜማውን ጭምር እያስታወስኩ ነው። በዚያ ቃል የተናገረ የሆነ የአካባቢያችን ሰውዬ ይመጣብኛል። ዓረፍተ ነገሩን የማነበው በዚያ ሰውዬ ዜማ ነው። ለምሳሌ፤ አንድ ቦታ ላይ ‹‹ከዚያ ምን ትመጣለች? እብድ። ›› የሚል አገላለጽ አግኝቼ ‹‹በዚህ እኔ በማውቀው ዜማ ያነቡት ይሆን?›› ብዬ አስቤያለሁ። ዜማ እኮ አይደለም! ምን ልበለው? ብቻ የሆነ የራሱ ቃና ያለው አነጋገር አለ። መልሱን የሚመልሰው ራሱ ጠያቂው ነው። እንዲህ አይነት ወጎችን አምቆ የያዘ ነው።

በከተማ ቦታ ቀልድ አዋቂ ሰው ካለ መተዳደሪያው ነው። ነገር አዋቂ፣ መልስ የሚዋጣላቸው ሰዎች፣ አገላለጻቸው አስቂኝ የሆነ... ሰዎች ብርቅ ስለሚሆኑ ነው መሰለኝ ይደነቅላቸዋል። በሀገር መሪ ደረጃ ሳይቀር (ለምሳሌ አቶ መለስ ዜናዊ) የሚናገሩት መልስ አስቂኝ ስለሚሆን በማህበራዊ ገጾች ለቀልድ ተብሎ ይዘዋወራል። ገጠር ውስጥ ግን ብዙ እንዲህ አይነት ሰዎች አሉ። ወግና ጨዋታ ወዲህ ደግሞ አሽሙር ይችሉበታል። በነገር ወጋ ያደርጋሉ። ሸሙኔ የእነዚህን ሰዎች አሽሙር ሁሉ ሳይቀር ነው የነገረን። ለምሳሌ፤ ስብሰባ ውስጥ ካድሬው በድምጽ ማጉያ (ማይክራፎን) ሲናገር አንዷ ተሰብሳቢ ከጎኗ ላሉ ሰዎች ‹‹አፉ አንሶን ደግሞ ድምጽ ማጉያ ጨመረበት!›› ትላለች። ይህን አሽሙር የተናገረችው ምናልባትም የካድሬው ድምጽ ከሌሎች የበለጠ ትልቅ ሆኖ ሳይሆን፤ ንግግሩ ውሸት እና አሰልቺ ስለሚሆን እንደ ጩኸት ስለሚያዩት ነው። መስማት ስለማይፈልጉ ነው። እንዲህ አይነት አሽሙረኞችም ናቸው።

ስብሰባ ላይ ማጨብጨብ የተለመደ ነው። የሸሙኔ ወገኞች ግን ይህ አዲስ ሆኖባቸዋል። እነርሱ ጭብጨባን የሚያውቁት ለዘፈን ወይም ለመዝሙር ነው። ለዚህም ነው ‹‹አጨብጭቡ›› ሲባሉ ‹‹እኛ ያለዘፈን ጭብጨባን የምናውቀው ለእርግማን ነው›› ያሉት። ስብሰባ እርግማን ነው እያሉ ይሆን? የሸሙኔ ሰዎች አሽሙረኛ ስለሆኑ ማን ያውቃል!

ሸሙኔ ታሪክም ነው። የቋንቋ ታሪክ። ዘመን የየራሱ ባህሪ አለው። የየራሱ ቀለም አለው። ይህን ግን በጽሑፍ ውስጥ አናገኘውም። ምክንያቱም በብዛት የሚጻፈው የተማረ የሚባለው የህብረተሰብ ክፍል በሚኖርበት ከተማ ውስጥ ያለው ሁኔት ነው። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ገላጭ ቃላት ባክነው ቀርተዋል። ‹‹ቀንኛ›› የሚለውን ቃል ሸሙኔ ውስጥ ሳገኘው፤ ‹‹ይሄ ነገር ግን ለምን በሀገር አቀፉ አማርኛ ውስጥ አልታወቀም?›› አልኩ። ቀንኛ ማለት ቀን የሚበላ (ምሳ) ማለት ነው። በእኛ አካባቢ ቁርስ የሚባል ቃል አይታወቅም። ቁርስን ተክቶ የሚያገለግለው ቃል ምሳ ነው። በአጭሩ፤ በጠዋት የሚበላው ምሳ፣ ቀን የሚበላው ቀንኛ የሚባል ሲሆን ማታ የሚበላው ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚታወቅበት ስም እራት ይባላል። ቀንኛን እንዳይታወቅ እና አካባቢያዊ ዘዬ ብቻ ሆኖ እንዲቀር ያደረገው የተጻፈላቸውና የተነገረላቸው ሌሎች ስለሆኑ ነው። ቋንቋ ደግሞ ማህበረሰባዊ ስምምነት ስለሆነ በብዛት በሚነገረው ነው። ሸሙኔ ግን በራሳቸው በገጸ ባህሪያቱ አካባቢያዊ ቃላት ስለሚነግረን የቋንቋ ጥናት ታሪክም ይሆናል።

አንድ ግራ የገባኝ አገላለጽ ግን አለ። የአክብሮት ስም (አንቱታ) ሲጠቀም ‹‹እርሳቸው›› መሆን የሚገባውን ‹‹እርስዎ›› በሚል ይገልጸዋል። ለምሳሌ፤ ‹‹ገበያ የዋሉም አይመስሉ አያ ጉልላት›› አልኩዎ እንደደረስኩብዎ (ገጽ 112)። ›› ይላል። ከዓውዱ መረዳት እንደሚቻለው ለማለት የተፈለገው ‹‹አልኳቸው እንደደረስኩባቸው›› ነው። ‹‹አልኩዎ፣ እንደደረስኩብዎ›› ሲል ለራሱ ለባለቤቱ የሚናገር ይመስላል። እየነገረን ያለው ግን ለእኛ ለተደራሲያን ነው።

ትረካው በአንደኛ መደብ ስለሆነና ራሱ ሸሙኔ ስለሚተርከው የሸሙኔ ዘዬ ይሆን? ምናልባት በዚያ አካባቢ ያሉ ሰዎች የአክብሮት ስም የሚጠቀሙት በዚሁ አገላለጽ ሆኖ ይሆን? እንዲያ ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ።

ምንም እንኳን በዓውድ መረዳት ቢቻልም ለአንዳንድ ቃላት ግን የግርጌ ማስታወሻ ቢኖራቸው ጥሩ ነበር። ለስነ ጽሑፋዊ ውበት ጥሩ ላይሆን ይችላል። ስነ ጽሑፍ ማብራሪያና ገለጻ ሲበዛበት ጥሩ አይደለም ይባላል፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ነገሮችን ግልጽ ለማድረግ በቅንፍ ውስጥ ይጠቀማል። ስለዚህ የመፍቻ ቃላት ቢኖሩ ጥሩ ነበር።


መጽሐፉ ከስነ ጽሑፍነት ባሻገር የባህልና የቋንቋ ጥናት የሚያደርጉ ሰዎች ሊያነቡት የሚገባ ነውና አንብቡት!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ጉብዝና ያሸልማል!

**አስናቀ ፀጋዬ**




የበርካታ ተማሪዎች የሂሳብ ትምህርት ውጤት ዝቅተኛ እንደሆነ ይነገራል። ሂሳብ ብቻ ሳይሆን ፊዚክስም ቢሆን ብዙ ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት ሚያገኙበት የትምህርት ዓይነት ነው። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት ከትምህርት ሚኒስቴር የወጡ የፈተና ውጤት ትንተና መረጃዎች አመላክተዋል። በሁለቱ የትምህርት አይነቶች ዝቅተኛ ውጤት ለመመዝገቡ ታዲያ የተለያዩ ምክንያቶች ይቀርባሉ። የትምህርት አሰጣጥ ሥነዘዴው ቀላል አለመሆን፣ መምህራን ትምህርቱ የሚሰጡበት መንገድ ውስብስብ መሆን፣ በተማሪዎችም በኩል ትምህርቱን አክብዶ ማየትና ሌሎችም ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

በርግጥ ጨወታ ተኮር የማስተማር ሥነ ዘዴ ተማሪዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በቀላሉ እንዲረዱ የሚያደርግ መሆኑ በተባበሩት መንግሥታት ትምህርት ክፍል ጭምር የሚመከር ነው። እንዲያም ሆኖ ግን የሂሳብ ትምህርት አሁንም ቢሆን ለብዙ ተማሪዎች የሚከብድና ከፍተኛ ውጤት የሚገኝበት የትምህርት አይነት አይደለም። ፊዚክስም እንደዛው። ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው እንግዲህ ተማሪዎች የሂሳብ ትምህርት ቀላል መሆኑን ተረድተው ውጤት እንዲያመጡ ለማበረታታት ማይ ሶሮባን ኢትዮጵያ የተሰኘው ተቋም «ጉብዝና ያሸልማል!» በሚል መሪ ሃሳብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተማሪዎችን በሂሳብ ትምህርት አወዳድሮ መሸለም የጀመረው።

አቶ ከበደ አጥናፉ የማይ ሶሮባን ኢትዮጵያ መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ተቋሙ ሶስት ሥራዎችን በዋናነት ያከናውናል። አንዱ እድሜያቸው ከስድስት እስከ አስራ ሶስት ዓመት የሆናቸው ልጆችን የሂሳብ ትምህርት/አባከስ/ ሥልጠና ይሠጣል። ሁለተኛ ሀገር አቀፍ የሂሳብ ትምህርት ጥያቄና መልስ ውድድር ያካሂዳል። ሶስተኛ ደግሞ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ምን ያህል የሂሳብ ጥያቄዎችን መመለስ ይቻላል የሚል የሂሳብ ውድድሮችን ያደርጋል።

ከነዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛ የሂሳብ ትምህርት የጥያቄና መልስ ወድድር ሲሆን በ2016 ዓ.ም በሃምሳ የኢትዮጵያ ከተሞች የሚገኙ ተማሪዎችን በማሰባሰብ ሲያወዳድር ቆይቷል። የሂሳብ ትምህርት ይከብዳል የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቀየር «ጉብዝና ያሸልማል» በሚል መሪ ሃሳብም ነው ውድድሩን ሲያካሄድ የቆየው። የሂሳብ ትምህርት የጥያቄና መልስ ውድድሩ ሲከናወን የነበረው በአምስት ዙር ነበር።

የመጀመሪያው ዙር የሂሳብ ትምህርት የጥያቄና መልስ ውድድር በየከተሞቹ ነበር የተከናወነው። በቅድሚያ በየከተማው ለሚገኙ ትምህርት ፅህፈት ቤቶች ደብዳቤ ከተላከ በኋላ ትምህርት ፅህፈት ቤቶቹ በውድድሩ ላይ ተማሪዎቻቸው እንዲሳተፉ ሲፈቅዱ የአንደኛው ዙር የጥያቄና መልስ ውድድር በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተዘጋጁ የሂሳብ ጥያቄዎች በየከተሞቹ እንዲላክ ይደረጋል።

በመቀጠል ተማሪዎች አንደኛውን ዙር የትምህርት ቤት ማጣሪያ ውድድር በየትምህርት ቤቶቻቸው ያካሂዳሉ። ይህንን የማጣሪያ ውድድር ያለፉ ተማሪዎች ሁለተኛ፣ ሶስተኛና አራተኛ ዙር ውድድር ካደረጉ በኋላ በከተማ ደረጃ ማእከል ተዘጋጅቶ ተማሪዎቹ ውድድራቸውን ያካሂዳሉ። ውድድሩም የሚካሄደው ከሶስተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ደረጃ ባሉ ተማሪዎች መካከል ነው። ለማወዳደሪያ ጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋም መንግሥት ለማስተማሪያነት በሚጠቀማቸው ቋንቋዎችና መፅሃፍቶች መሠረት ነው። ተማሪዎቹም በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉና እነርሱ በሚገባቸው ቋንቋዎች ውድድራቸውን አካሂደዋል። ይህም ሀገሪቷ ላይ ባሉ ቋንቋዎች ሁሉ ተማሪዎች የሂሳብ ትምህርት ጥያቄና መልስ ውድድር ሲያካሂዱ የሂሳብ ትምህርት ቋንቋዊ ውበትንም ያሳያል።

አምስተኛው ዙር የተጠናቀቀውና የከተማ መዝጊያ የተሰኘው ውድድር ሲሆን በዚህ ውድድር ተማሪዎች ከየከተማው ከተማቸውን ወክለው ወደ ሀገር አቀፍ ውድድር የሚያልፉ ተማሪዎች የሚለዩበት ነው። ስድስተኛውና የመጨረሻው ውድድር ደግሞ ከሀምሌ 28 እስከ ነሃሴ አንድ 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ በቅርቡ ተካሂዷል። ከየከተሞቹ የመጡት የከተማ አሸናፊ ተብለው የተለዩ 4ሺህ ተማሪዎች የመጨረሻውን ስድስተኛ ዙር የጥያቄና መልስ ውድድር አካሂደዋል። በውድድሩ አሸናፊ ለሆኑ ተማሪዎችም የአራት ሚሊዮን ብር የገንዘብና የአይነት ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። ባያሸንፉም ከተማቸውን ወክለው ለተሳተፉ ተማሪዎችም የሜዳልያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

ስራ አስኪያጁ እንደሚያብራሩት የእንዲህ አይነቱ የጥያቄና መልስ ውድድር ዋና ዓላማ ሂሳብ ትምህርት ይከብዳል የሚለውን አመለካከት ለማስወገድና ጉብዝና እንደሚሸልም መልእክት ለማስተላለፍ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ውድድር ዓላማ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሂሳብ ትምህርት ውድድር በኦሎምፒክ ላይም ጭምር ስላለ በዚህ የሂሳብ ትምህርት ኦሎምፒክ ውድድር ላይ ኢትዮጵያ እየተሳተፈች ባለመሆኑ በሂሳብ የተሻሉ ተማሪዎችን በመምረጥ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## በጋዛው ጦርነት ላይ የተኩስ አቁም ስምምነት ከተደረሰ ኢራን በእሥራኤል ላይ ጥቃት ከመፈጸም እንደምትታቀብ አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ኢራን የጋዛው ጦርነት ላይ የተኩስ አቁም ስምምነት የሚፈጸም ከሆነ በእስራኤል ላይ እሰነዝረዋለሁ ያለችውን የአጸፋ ምላሽ እንደምታጤነው አስታወቀች፡፡

የሀገሪቱ የደኅንነት ተቋም ከፍተኛ ባለሥልጣን ለሮይተርስ እንደተናገሩት ቴልአቪቭ በኢራን ሉዓላዊ ክልል ውስጥ በመግባት ለፈጸመችው ወንጀል ማካካሻው የተኩስ አቁም ስምምነት ብቻ ነው ብለዋል፡፡

የሀማስ የፖለቲካ ቢሮ ኃላፊ እስማኤል ሀኒየህ ግድያን ተከትሎ ቴሄራን በዓይነቱ ከፍተኛ የተባለ ቀጥተኛ ጥቃት በእሥራኤል ላይ እንደምትፈጽም ለሳምንታት ስትዝት ቆይታለች፡፡

የደኅንነት ባለሥልጣኑ ኢራን ከቀጠናው አጋሮቿ ጋር በመሆን ለተፈጸመው ጥፋት ተመጣጣኝ ርምጃ ለመውሰድ በቂ ዝግጅት አድርጋ ማጠናቀቋን አስታውቀዋል፡፡

በዛሬው ዕለት በኳታር ወይም በግብፅ በሀማስ እና እሥራኤል መካከል የተኩስ አቁም ስምምነት ድርድር ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል፤ ይሁንና ኢራን የአጸፋ ምላሽ ከመስጠቷ በፊት ለድርድሩ ሂደት ምን ያህል ጊዜ እንደምትታገስ በይፋ አላሳወቀችም፡፡

የነጩ ቤተ መንግሥት ቃል አቀባይ ጆን ኪርባይ በዚህ ሳምንት ኢራን የዛተችውን ጥቃት ልትፈጽም እንደምትችል የደኅንነት መረጃዎች ማመላከታቸውን ከትናንት በስቲያ በነበራቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተናግረዋል፡፡

አክለውም የአጸፋ ምላሹ የተኩስ አቁም ስምምነቱ ከመካሄዱ ወይም ውጤቱ ከመታወቁ በፊት የሚደረግ ከሆነ የድርድር ሂደቱ ላይ ጥላ እንደሚያጠላ ነው ቃል አቀባዩ የተናገሩት፡፡

የእስራኤል የመከላከያ ሚኒስትር ዮቭ ጋለንት በበኩላቸው በቴህራን እና በቤሩት የሚገኙ ሁኔታዎችን በቅርበት እየተከታተልን ነው፤ ጥቃት ሊሰነዘር የሚችለበትን ሁኔታ እና ዒላማ ላይ ቅድም ዝግጅት አድርገናል ብለዋል፡፡

በቅርብ ሳምንታት በቀጠናው እያየለ የመጣውን ውጥረት ለማርገብ አሜሪካ የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ስትሆን ቱርክን ጨምሮ ሦስት የአካባቢው ሀገራት ቴህራን ውጥረቱን ከሚያባባስ የአጸፋ ምላሽ እንድትታቀብ እንዲያግባቡ ኃላፊነት ሰጥታለች፡፡

ሮይተርስ እንደዘገበው ኢራን በዚህ የአጸፋ ምላሽ ማስፈራሪያ የጋዛውን ጦርነት ማስቆም የምትችል ከሆነ ከፍተኛ ድል የሚጎናጽፉት ነው። ሆኖም ይህ የማይሳካ ከሆነ ቀጣናዊ ግጭት እንዲቀሰቅስ ባትፈልግም በቴልአቪቭ ላይ ጥቃት ከመሰንዘር ወደ ኋላ አትልም፡፡

ከዚህ ባለፈም ኢራን በድርድር ሂደት ላይ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የጎንዮሽ ስብሰባዎች እና የዲፕሎማሲ ጥረቶች ላይ ተሳትፎ እንዲኖራት ትፈልጋለች ተብሏል፡፡

ከትናንት በስቲያ አሜሪካ፣ ብሪታንያ፣ ፈረንሳይ እና ጣሊያን ጥቃት ከመሰንዘር እንድትታቀብ ጥሪ

## ቻይና የኤሌክትሪክ መኪናን በ10 ደቂቃ መሙሳት የሚያስችል ቻርጀር መሥራቷን ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቻይና የኤሌክትሪክ መኪናን በ10 ደቂቃ መሙላት የሚያስችል ቻርጀር መሥራቷን ገለጸች፡፡

በዓለማችን ላይ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ፍላጎት እና ምርት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይሁንና እነዚህን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እንደ ልባቸው ሊስተናገዱበት የሚችሉት ቻርጀር ማግኘት አዳጋች ሆኗል፡፡

ሌላኛው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ቻርጅ ለማድረግ የሚፈጀው ጊዜ ረጅም መሆን ሲሆን በየጊዜው እየተሻሻለ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡

የቻይናው ዚከር የቴክኖሎጂ ኩባንያ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን በቶሎ ቻርጅ ለማድረግ መላ አግኝቻለሁ ብሏል፡፡

ኩባንያው እንዳስታወቀው አንድን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባትሪን በ10 ደቂቃ ውስጥ 80 በመቶ መሙላት የሚያስችል ቴክኖሎጂ መስራቱን አስታውቋል፡፡

የአሜሪካው ቴስላ ኩባንያ አንድን ተሽከርካሪ በ15 ደቂቃ ባትሪ መሙላት የሚያስችል ቻርጀር በማምረት በገበያ ላይ አስተዋውቋል፡፡

የዓለማችን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባትሪ የሚሞላበትን ጊዜ ለማሳጠር በሙከራዎች ላይ ሲሆኑ የዓለም ገበያን እየተቆጣጠሩ የመጡት የቻይና ኩባንያዎች አዲስ ፈጠራ ይፋ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

የቻይና ኩባንያዎች የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን በማምረት እና ተያያዥ የሆኑ አዳዲስ ፈጠራዎችን ለዓለም ገበያዎች በማቅረብ ዋነኛ ተወዳዳሪ የሆኑ ሲሆን አሜሪካን እና አውሮፓ ኅብረትን ጨምሮ በርካታ ሀገራት የቻይናን ግስጋሴ ለመቆጣጠር የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡

ባሳለፍነው ግንቦት ወር ላይ የእንግሊዙ ኒዮቦልት የቴክኖሎጂ ኩባንያ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን በቶሎ ቻርጅ ለማድረግ መላ አግኝቻለሁ ማለቱ አይዘነጋም፡፡

ኩባንያው እንግዶች በተገኙበት በአራት ደቂቃ ውስጥ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባትሪን እንደሚሞላ አረጋግጧል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

በሙከራ ደረጃ ያለው ይህ ቴክኖሎጂ በ2025 በገበያ ላይ እንደሚውል ይጠበቃል፡፡

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# አረንጓዴ ዐሻራን ተቋማዊ የማድረግ ወሳኝ ርምጃ፤

ሰሞኑን እንኳ አውሮፓ በከፍተኛ ሙቀት እየተንገበገበች ነው። የዓለማችን የሰው ሥራሽ ቅርሶችና የቱሪስቶች መናኸሪያ የሆነችው የግሪክ መዲና አቴንስ በዙሪያዋ በተቀሰቀሰ ሃይለኛ ሰደድ እሳት ህልውናዋ አደጋ ተደቅኖበት ሰነባብቷል። ጎረቤት ሀገራትን ድረሱልኝ እስከማለት ደርሳ ነበር። የአማልክቶቿ አምላክ አዳናት እንጂ። ሆኖም ስጋቱ እንዳለ ነው። አሜሪካን ሌላ ሱናሚና ኤርንስቶ የተሰኘ ሀሪካን መጣሁ መጣሁ እያላት ነው። የጃፓኗ ቶኪዮ ደግሞ ሃይለኛ ውሽንፈር እንዳይመታት ተሰግቷል።

ምስራቅ አፍሪካዊቷ ሀገረ ኢትዮጵያ ደግሞ የአየር ንብረት የደቀነውን አደጋ አበክራ በመገንዘብ በየአመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ችግኝ በነቂስ ወጥታ እየተከለች ነው። የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን ለመቋቋም የሚደረጉ ዓለም አቀፍ ጥረቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ሚናዋን አጠናክራ ትወጣለች። የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከዓለም አቀፉ የአረንጓዴ ዕድገት ኢንስቲትዩት፣ ከግብርና ሚኒስቴር እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሰሞኑን ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)፥ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብሩ የሀገሪቱን የደን ሽፋን በ2011 ዓ.ም ከነበረበት 17 ነጥብ 2 በመቶ ዘንድሮ ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ አሳድጎታል ብለዋል። አረንጓዴ ዐሻራ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ስለሆነ አጠናክሮ ለማስቀጠል ይሠራል ማለታቸውን ኢዜአ መዘገቡ ለዛሬ መጣጥፌ መነሻ ሆኖኛል።

ባለፉት ዓመታት በተጀመረው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በኢትዮጵያ በሁሉም ክልሎች በመጀመሪያው ምዕራፍ ከ32 ቢሊዮን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን የተተከሉት ችግኞችም በዘርፉ ሙያተኞች በተደረጉት ክትትል 90 በመቶ ለመፅደቅ ችለዋል። የተፈጥሮ ሀብትና የሕይወታዊ ሀብት ጥበቃ ሥራ ሲጠናከርና ተከታታይነት ባለው መንገድ ሲሠራ ከአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ ነጻ የሆነና መልካምድራዊ አቀማመጥን መሠረት ያደረገ አካባቢያዊ የአየር ንብረት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ዕድል ይሰጣል። በመጀመሪያው ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በመላ ሀገሪቱ በተተከሉ ችግኞች ቀደም ሲል ተራቁተው የነበሩና የአፈር መሸርሸር አጋጥሟቸው የነበሩ አከባቢዎች በአሁኑ ወቅት ወደ ቀድሞ ገጽታቸው እየተመለሱና መሬቱም እያገገመ መሆኑን የግብርና ባለሙያዎች ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው። የአረንጓዴ ዐሻራ በተለያዩ ዘርፎች ውጤቶችን እያሳየን ነው።

ተደጋጋሚ ድርቅ ሲያጠቃቸው የነበሩ አካባቢዎች ዝናብ ማግኘት ጀምረዋል፣ የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ ተችሏል፣ የደረቁ ምንጮችና ሀይቆች እንደገና ቀድሞ ወደ ነበሩበት መመለስ ችለዋል፣ ለበጋና የመኸር እርሻ ተስማሚ የሆነ ዝናብ ማግኘት ተችሏል። ከሥራ እድል ፈጠራነት አንጻር ለእንስሳት መኖነት፤ ለንብ ማነብ ፤ ለካርቦን ሽያጭና ለጎረቤት ሀገራት መልካም ጉርብትና እና የዲፕሎማሲ ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በተያዘው መኸር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ 7 ነጥብ 2 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል እርብርብ እየተደረገ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞችን መትከል በተለያዩ መስኮች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። የተወሰኑትን በወፍ በረር እንቃኝ። ዛፎች ካርቦን ዳይኦክሳይድን ከከባቢ አየር ውስጥ ስለሚወስዱ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ፤ ለተለያዩ የእፅዋትና የእንስሳት ዝርያዎች መኖሪያ በማመቻቸት የብዝሀ ሕይወትን ለመደገፍ፤ የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል እና የአፈር ለምነትን ለማሻሻል ስለሚያግዙ ግብርናውን ዘላቂ ያደርገዋል።

የአሜሪካ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (EPA) ፤ በአማካይ አንድ ዛፍ በዓመት 22 ኪሎ ግራም ካርቦን ዳይኦክሳይድን ከከባቢ አየር ሊሰበስብ ይችላል ይለናል። በሀገራችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከተተከሉ ወደ 40 ቢሊዮን ከሚጠጉ ችግኞች ወደ 30 ቢሊዮን የሚጠጉት ጸድቀዋል። ወደ ዛፎች ያድጋሉ ብለን ብናስብ እና እያንዳንዱ ዛፍ 22 ኪሎ ግራም ካርቦን በዓመት ቢሰበስብ፤ በየአመቱ 660,000,000,000 ኪግ ካርቦን ዳይኦክሳይድ ወይም 660,000,000 ሜትሪክ ቶን ካርቦን ዳይኦክሳይድ መሰብሰብ ወይም ካርቦን ማምረት ችለናል ማለት ነው። በተገባልን ቃል መሠረት ይሄን ካርቦን ብንሸጥ ብዙ ሚሊዮን ዶላሮችን አገኘን ማለት ነው። ይሄን ከአካባቢ ጥበቃ ጥቅሙ ጋር ስናሰላው አዋጭ ነው። ለነገሩ ሁለተናዊ ጥቅሙ ከገንዘብ በላይ መሆኑ ሳይዘነጋ።

የችግኝ ተከላ የሥራ እድል በመፍጠር፤ ዘላቂ የሆነ የእንጨት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት እንዲኖር፤ የአረንጓዴ ልማትና የብዝሀ ሕይወት መጨመር ቱሪስቶችን በመሳብ በቱሪዝም ዘርፍ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዲመጣ፤ ብክለትን በመቀነስ አየሩን በማጣራት ለሕዝቡ የተሻለ የአየር ጥራት እና የተሻሻለ የአተነፋፈስ ጤንነትን እውን ለማድረግ፤ ዛፎች የውሃ ተፋሰስን ዘላቂ በማድረግ አስተማማኝ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር ከማገዝ ባሻገር የችግኝ ተከላ የዜጎችን የልማት ተሳትፎ ሊያዳብር ይችላል። ብዙ ዛፎች የአካባቢን የአየር ንብረት ለመቆጣጠር፣ የሙቀት መጠንን ለመቀነስ እና ለአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል፤ እንደ ጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት ያሉ የተፈጥሮ አደጋዎችን ተፅእኖ በመቀነስ የአፈር መከላትን በማስቀረት የውሃ ፍሰትን ለመቆጣጠር፤ እንዲሁም የደን ልማትን ማስተዋወቅ ለገበሬዎች ተጨማሪ የምግብ፣ የእንስሳት መኖ እና የገቢ ምንጭ በማቅረብ የምግብ ዋስትናን በማጎልበት አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ይዞ ለመነሳት እምቅ አቅም አለው።

ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ችግኝ ተከላ የአየር ንብረት ለውጥን ፤ የዓለም ሙቀት መጨመርንና የአካባቢ ጥበቃ ችግሮቻችንም ሆነ ድህነትን ፤ የምግብ ዋስትና ጎድለትን ፤ የምርታማነት ተግዳሮትን ፤ ድርቅን ፤ ርሃብን ፤ የዝናብ መቆራረጥንና መቅረት ፤ የውሃ እጥረትን ፤ የኑሮ ውድነትን ፤ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና በምርት አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተትት ፤ ሥራ አጥነት ፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ፤ የጸጥታና የደህንነት ችግርን ፤ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማሳለጥ እና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማለም መስፈንጠሪያ በመሆን ያገለግላል ። ቀደም ባለ አንድ መጣጥፌ ችግኝ ተከላን የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ማስተር ኪይ ነው ያልሁት በዚህ የተነሳ ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ደጋ የነበሩ ወይና ደጋ ፤ ወይና ደጋ የነበሩ ቆላ ፤ ቆላ የነበሩ በርሃ ፤ በርሃ የነበሩ አካባቢዎች እንደ ሳህራ እጅግ በርሃማ እየሆኑ ነው። አመት እስካመት ይገማሸሩ የነበሩ ወንዞች ፤ በየገመገሙ ፤ በየጋራና በየሸንተረሩ ይንፎለፎሉ የነበሩ ምንጮች ደርቀዋል። ወደ 60 በመቶና ከዚያ በላይ የነበረው የደን ሽፋን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከሶስት በመቶ የማይበልጥ ነበር። አሁን በተደረገ ርብርብ የደን ሽፋኑን ወደ 17 በመቶ ከፍ ብሏል። በአየር ንብረት ለውጡ የተነሳ በየአስር አመቱ ይከሰት የነበረው ድርቅ በየአመቱ ከመመላለሱ ባሻገር በበልግና በመኸረም መከሰት ጀምሯል። ከአመት አመት ይከሰት በነበረ የዝናብ እጥረት የተነሳ የከረሰና የገጸ ምድር ውሃ እጥረት ተከስቷል።

እየተቆራረጠና እየተዛባ የሚጥለውን ዝናብ ቢሆንም ደኖች በመራቆታቸው የተነሳ አፈሩ ውሃ መያዝ ባለመቻሉ ጠብ ባለ ቁጥር ስለሚሸረሸር የአፈር መከላትን እያባባሰ ግብርናውን አደጋ ላይ ጥሎታል። በዚህ የተነሳ ከሕዝብ ብዛቷ አንጻር ተመጣጣኝ ምርት ማምረት አልቻለችም ። የግብርና ቴክኖሎጂ ምርጥ ዘር ፤ ማዳበሪያ ፤ ፀረ አረምና ተባይ ኬሚካል በመጠቀም ምርትን ለማሳደግ የተደረገው ጥረት አይደለም አግሮ ኢንዱስትሪውን ዜጋውን መመገብ ተስኖት ነበር። በቅርብ የወጡ ጥናቶች 47 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የከፋ የምግብ እጥረት እንዳለባቸው ያትታሉ። በቅርብ ይፋ የሆኑ መረጃዎች ዛሬም በሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የምግብ እህል ርዳታ እንደሚያስፈልገው የተገለጸ መሆኑ ፈተናውን ገና እንዳልተሻገርነው ያመለክታል።

የዓለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ የመጣው የአየር ንብረት ለውጥ ለሀገራችንም ሆነ ለአፍሪካ ጥሩ ዜና የለውም። እየታረሰ የነበረው መሬት ለምነቱን በማጣቱና በመራቆቱ የተነሳ እየቀነሰና እየተራቆተ ይገኛል ። ግብርና ለሀገሪቱ ጥቅል ብሔራዊ ምርት ድርሻው 47 በመቶ ቢሆንም ፤ መታረስ ካለበት መሬት 17 በመቶ ብቻ ነው እየታረሰ ያለው ። ይህ በሌላ በኩል እርስ በርሱ የሚቃረን ይመስላል ። የከፋ የምግብ እህል እጥረት ፣ ድህነትና የበዛ ሥራ አጥ ባለበት ሀገር መታረስ የሚገባው 83 በመቶ መሬት ጦም ያድራል።

አበው የወለፈንዲ ስልቻ ጤፍ ይቋጥራል ፣ ባቄላ ያፈሳል እንዲሉ። ከቅርብ አመታት ወዲህ ሀገራችንን ጨምሮ በዓለማችን እያየናቸው ያሉ የደን ቃጠሎዎች ፣ ድርቅ ፣ ጎርፍ ፣ ውሽንፍር ፣ የበርሃ መስፋፋት ፣ የወቅቶች መዛነፍ ፣ ወዘተረፈ የዓለም ሙቀት መጨመር እነ ትራምፕ እንደሚሊቱ የደባ ኅልዮት ሳይሆን የእለት ተእለት የሕይወት ገጠመኝ ከሆነ ውሎ አድሯል ። የበለጸጉ ሀገራት ዛሬ ድሀ ሀገራትን ዋጋ እያስከፈለ ባለው የኢንዱስትሪ አብዮት ባካበቱት ሀብት እየተቋቋሙት ሲሆን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ግን በዓለም ሙቀት መጨመር ያለእዳቸው ውድ ዋጋ እየከፈሉ ነው። በግብርናችን ያለ መዋቅራዊና ተቋማዊ ችግር የራሱ ድርሻ ቢኖረውም የዓለም ሙቀት መጨመር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ ጋሬጣ እየሆነ ይገኛል።

ግብርናችን ዛሬም ከበሬ ጫንቃ ያልወረደ ፣ በተበጣጠሰ መሬት ላይ የተመሠረተ ፣ የግብርና ቴክኖሎጂውም በተለይ የማዳበሪያና የምርጥ ዘሩ አቅርቦቱ የየአካባቢውን ሥነ ምህዳርን ከግምት ያላስገባ ስለነበር ከሞላ ጎደል የገጠር ልማት ፖሊሲው የታለመለትን ያህል ውጤታማ ሊሆን ባለመቻሉ ዛሬም ከተመፅዋቾችነት ሊያወጣን አልቻለም ። ዛሬም በቀን ሶስት ጊዜ መመገብ አልቻልንም ። ይሁንና በተለይ ካለፉት ዓመታት ወዲህ የኩታ ገጠም ግብርናን ፣ በተወሰነ ደረጃ ሥነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረገ የቴክኖሎጂ እገዛ ፣ የከርሰና የገጸ ውሃን አሟጦ የመጠቀም ፣ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ለመሥራት ፣ የከተማ ግብርና ትኩረት ማግኘቱ ፤ በአርብቶ አደሩ የሚገኙ ጦም ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ ለማልማት አበረታች ጥረትና ርብርብ መደረጉ እና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ማስቀረት መቻሉ ግብር ከምግብ ዋስትና ባሻገር ተስፋችንን እንድናድስ አድርጎናል ።

ቀደም ባለ መጣጥፌ እንዳልሁት ችግሮቻችንን ሁሉ ፈታተን ፣ በታትነንና አገላብጠን ብንመረምራቸው አብዛኛዎቹ ከአንድ ቅርጫት የሚገኙ ናቸው ። የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ ካለመንከባከብ ፣ ካለመጠበቅና ካለማልማት ። የዓለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ በመጣ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የተፈጥሮ ሀብታችን እየተጎሳቆለ በመምጣቱ ማለትም መሬታችን የተራቆተ ፣ ዝናባችን የአጠረና የተቆራረጠ በመሆኑ የከርሰና የገጸ ምድር ውሃችን በመመናመኑ ግብርናው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም ። በዚህ የተነሳ በግብርና ላይ የተመሠረተው የዜጋው ሕይወት ፤ የሀገሪቱ ልማት ችግር ላይ ወድቆ ቆይቷል።

ይህ የሀብት ውስንነትን ፈጥሯል ። በዚህ የተነሳ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከዓመት ዓመት እየተባባሱ መጡ ። እነዚህን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችን እንዲያገግም ሌት ተቀን መሰራት አለበት ። መሬት ማገገም ፣ ውሃ መያዝ አለበት። ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው ችግኝ በመትከልና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን በስፋት በማከናወን ነው ። “ አረንጓዴ ዐሻራ “ የበሽታውን ምልክት ከማከም ይልቅ መነሻውን በማያዳግም ሁኔታ የመፈወስ አቅም እንዳለው በማመን ነው ፤” አረንጓዴ ዐሻራ ! “ የእንቆቅልሾቻችን ሁሉ መፍቻ ቁልፍ (ማስተር ኪይ ) ነው ያልሁት ።

መንግሥትም ለዚህ ይመስላል አረንጓዴ ዐሻራ ከሀገሪቱ ዓመታዊ በጀት እስከ አንድ በመቶ ድርሻ እንዲኖረው የሚያደርግ ረቂቅ አዋጅ ለፓርላማ ያቀረበው። በየዓመቱ ከሀገር ውስጥ ገቢ ምንጭ ከሚመድበው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ከ0.5 በመቶ እስከ አንድ በመቶ ያህል፣ ለአረንጓዴ ዐሻራና ለተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድ እንዲሰጥ የሚደነግግ ረቂቅ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቀርቧል። ይህ ለአረንጓዴ ዐሻራ የተሰጠውን ትኩረትና ተቋማዊ እንዲሆን ስለመወሰኑ ፍንጭ ይሰጣል።

ሰኔ 13 ቀን 2016 ዓ.ም. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን 33ኛ መደበኛ ስብሰባ የቀረበው የአረንጓዴ ዐሻራና የተጎሳቆለ መሬት ማገገሚያ ልዩ ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ የሚል ስያሜ የተሰጠው ረቂቅ አዋጅ፣ ልዩ ፈንዱን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው የተቀናጀ ቋሚና ዘላቂነት ያለው የሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ በመመደብና በማሰባሰብ ሁሉም ክልሎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር መቀየስ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ እንደሆነ ያብራራል።


ልዩ ፈንዱ ዘጠኝ ዓላማዎች ሲኖሩት ከእነዚህም መካከል የተጎሳቆለ መሬት በተፈጥሮና በመልሶ ማልማት መርህ በመታገዝ እንዲያገግም በማድረግ፣ የደን ልማትና የደን መልሶ ማልማትን መደገፍ፣ የሀገሪቱን የካርቦን ልቀት ቅነሳ ግብ እንዲሳካ አስተዋጽኦ ማድረግ፣ እንዲሁም የከተማ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት ሥራዎችን መደገፍ የሚሉ ይገኙበታል። የልዩ ፈንዱ የፋይናንስ ምንጮች የመጀመሪያው የፌዴራል መንግሥት ከሚመድበው በጀት፣ በሁለተኝነት ደግሞ የልማት አጋሮች፣ የሲቪክ ማህበረሰቦች፣ እንዲሁም የግል ዘርፍ ከሚሰጡት ድጋፍ እንደሆነም በረቂቅ አዋጁ ተጠቅሷል።

የፌዴራል መንግሥት ከሚመድበው በጀት የሚሰበሰበው ገንዘብ ለልዩ ፈንዱ በተከፈተ የባንክ ሒሳብ በየሦስት ወሩ በገንዘብ ሚኒስቴር ተቀማጭ እንደሚሆን ሲገለጽ፣ በሁለተኛ ደረጃ ከሠፈሩት ምንጮች የሚደረገው ድጋፍ የሚተዳደርበት አኳኋን ደግሞ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመርያና የአሠራር ሥርዓት እንደሚወሰን ተብራርቷል። የልዩ ፈንዱን የሀብት ክፍፍልና አለቃቀቅ በተመለከተ የሠፈረው ድንጋጌ፣ መንግሥት የሚመድበው ዓመታዊ በጀት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ለፌዴራል መንግሥትና ለክልሎች ይደለደላል ይላል።

ለክልሎች ከሚደለደለው በጀት ላይ የእያንዳንዱን ክልል ድርሻ ለመወሰን የሚያገለግለውን የገንዘብ ሚኒስቴር አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ይቀርባል ሲል፣ ሆኖም ለመሸጋገሪያነት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያፀደቀው ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ ቀመር በጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ይገልጻል። በረቂቅ አዋጁ መሠረት ከተደለደለው ዓመታዊ የሀብት ድርሻ ላይ በየሦስት ወሩ ወደ ተጠቃሚ አካላት ገንዘብ ሊተላለፍ የሚችለው የሥራ አፈጻጸምን መሠረት በማድረግ፣ ክልሎች ተጓዳኝ በጀት ሲመድቡና በክልሉ ለሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ፈሰስ ሲያደርጉ ይሆናል ተብሏል።

ሻሎም።አሜን።

# ስፖርት



## የስፖርት ተቋማት ገለልተኝነት እስከምን ድረስ?

**ብርሃን ፈይሳ**

ትልቁ የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ በአራት ዓመት በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ውዝግቦች መነሳታቸው የተለመደ ጉዳይ ነው። ከአትሌቶች ምርጫ እስከ በርካታ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ንትርክ የማያጣው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ በቅርቡ በተጠናቀቀው የፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ አስቀድሞ በተነሱ ውዝግቦች ታጅቦ ተደምድሟል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ከሥራ አስፈፃሚ ምርጫ አንስቶ በበርካታ ጉዳዮች አካሄዱ ሕጋዊ እንዳልሆነ ሲተች ሰንብተል። ሀገር አቀፍ የስፖርት ሕግና ደንቦችን በመጣስ ብዙዎች ጥያቄ የሚያነሱበት ኮሚቴ ተገዢነቱ ከሀገር አቀፍ ሕጎች ይልቅ ለዓለም አቀፉ ደንቦች እንደሆነ በተደጋጋሚ በመግለፅም መንግሥት ጣልቃ መግባት እንደማይችል ትልቅ አጥር ሰርቶ በራሱ መንገድ ሲጓዝ እየታየ ይገኛል።

ስፖርቱን የሚመራው መንግሥታዊ አካልም እስካሁን ዝምታን መርጧል። በዓለም አቀፍ ጥላ ስር ያሉ የስፖርት ተቋማት ከሀገር አቀፍ ሕግ ጋር በምን መልኩ ይተገበራሉ? የተጣሱት ሕግና ደንቦችስ የትኞቹ ናቸው? መንግሥት ጣልቃ የማይገባውና የስፖርት ተቋማት ገለልተኝነትስ እስከምን ድረስ ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ለብዙዎች ግልፅ አይደሉም።

አቶ ታምራት በቀለ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ለ10 ዓመታት የጽህፈት ቤት ኃላፊ እና በዋና ጸሃፊነት አገልግለዋል። በለንደን እና ሪዮ ኦሊምፒኮች እንዲሁም በ2ኛውና 3ኛው የወጣቶች ኦሊምፒክ ላይ ሲሳተፉ፣ በሶስቱ የቡድን መሪ (ቺፍ ደሚሽን) በመሆን አገልግለዋል። ከሥራቸው ጋር በተያያዘም በዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን የመከታተል እንዲሁም ጉባዔዎች ላይ የመገኘት ብዙ ዕድል ነበራቸው። የዓለም አቀፉን ኦሊምፒክ ኮሚቴ ሕግና ደንብ ጠንቅቀው



**አቶ ታምራት በቀለ፣**

ከሚያውቁ ሰዎችም አንዱ ናቸው።

እንደ አቶ ታምራት ማብራሪያ፣ ብሄራዊ የኦሊምፒክ ኮሚቴዎች የሚመሠረቱት በብሄራዊ የስፖርት ማህበራት ሲሆን፤ ዕውቅና የሚሰጠውም ስፖርቱን በበላይነት በሚመራው መንግሥታዊ አካል (የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር) ነው። ይህም አካል በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራትን ይመዘግባል፣ እውቅና እና ፈቃድ ይሰጣል። በመሆኑም ኦሊምፒክ ኮሚቴም እንደሌላው የስፖርት ማህበር (ፌዴሬሽን) ሂደቱን ተከትሎ ይቋቋማል፤ ከዚያም ከዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ ቻርተር ጋር በሚጣጣም መልኩ ሥራውን ያከናውናል። ለአብነት ያህልም ኦሊምፒክን በሀገር ደረጃ ማስፋፋት፣ የኦሊምፒክ መርሆችን በደንቡ ውስጥ እንዲያካትት፣ በኮሚቴው ውስጥ አባል የሚሆኑ አካላት እነማን ናቸው የሚለውንና ወዘተ አሠራሮችን መከተል ይገባዋል። በዚህም መሠረት ብሄራዊ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ከዓለም አቀፉ ተቋም የሚቀዳቸው ሕጎች ቢኖሩም በዋናነት ግን በሀገር አቀፉ የስፖርት ሕግ የሚመራ ይሆናል።

ብሄራዊ ኮሚቴው በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና እና ፈቃድ ካልተሰጠው መንቀሳቀስ እንደማይችል የሚያስረዱት አቶ ታምራት፤ ከኢትዮጵያ ሕግ አንጻር ከታየ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና የውጪ ድርጅቶች ጭምር ሲቋቋሙ በሲቪል ማህበራትና ማደራጃ ምዝገባና ዕውቅና ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣሉ። የስፖርት ማህበራትም በየ 4 ዓመቱ የሚታደሱ ሲሆን፤ ሕግና ሥርዓት የማያከብሩ ደግሞ በመንግሥታዊ አካሉ እንቅስቃሴያቸውን እስከማስቆም የሚደርስ ርምጃ ሊወሰድ ይችላል። አሁን ከኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋር በተያያዘ በሚታየው ሁኔታ ግን መንግሥታዊው አካል በትዕግስት እያሳለፈው ያለ ይመስላል ይላሉ።

ከዚህ ባለፈ ዓለም አቀፉ ኮሚቴ የሚከለክላቸው ውስን ጉዳዮች ብሄራዊው ኮሚቴ ላይም ይተገበራሉ፤ ለአብነትም የመንግሥት ባለሥልጣናት የኮሚቴው ሥራ አስፈጻሚ እንዳይሆኑ ይከለክላል። በኢትዮጵያ ሕግ የማህበራት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሥራቸውን የሚያከናውኑት በአማተር በመሆኑ ባለሥልጣናት መሆናቸውን ላይከለክል ይችላል። ይሁን እንጂ ዓለም አቀፉ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የመንግሥት ባለሥልጣናትን (ተሿሚዎች) እንዲሁም በሕዝብ የተመረጡ አካላት በሥራ አስፈጻሚው መካተት እንደማይችሉ በቻርተሩ (ከገጽ 63-65) ላይ በግልጽ መቀመጡንም አቶ ታምራት ያነሳሉ። ይህም ማለት የክልል ስፖርት ቢሮ ኃላፊ የሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናትን የሚጨምር ነው። የሥልጣን ዘመንም ቢሆን ከ4 ዓመት መብለጥ የለበትም የሚል ሲሆን፤ ምናልባት የታመነበት ከሆነ ብቻ ከዚያ በላይ ሊቆይ ይችላል። ይህ ሁኔታ በዋናነት በኢትዮጵያ የስፖርት ማህበራት መመሪያ መሠረት ሲተገበር ኮሚቴውም እንደየትኛውም ፌዴሬሽን በዚህ ጥላ ስር ማለፉ የግድ ነው።

አቶ ታምራት እንደሚያስረዱት፣ የኦሊምፒክ ቻርተሩ እንዲተገበሩ ከሚያመላክታቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የምርጫ ጊዜ ከኦሊምፒክ መካሄድ በኋላ እንደሚደረግ ነው። የሀገር ውስጥ ደንቡም በተመሳሳይ ኦሊምፒክ ከተካሄደ እስከ 2 ወር ይደረጋል በሚል ያስቀምጠዋል። ምክንያቱም ለ4 ዓመታት የተከናወኑ ጉዳዮች ኦሊምፒክን ጨምሮ በወቅቱ የሚገመገም በመሆኑ ነው። ከዚያ ቀደም የሚደረግ ምርጫ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ የተደረገውም ሕገ ወጥ ምርጫ ነው። በመሆኑም ከቻርተሩ ጋር የሚጣረስ ነገር በመንግሥት (ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር) በኩል አይተግበር እንጂ ይህን በመሰለው ሕገወጥ አካሄድ ግን ርምጃ መውሰድ ይቻላል። ይህም በየትኛውም አካሄድ ሀገርን ሊያስቀጣ ወይም ሊያሳግድ የሚያስችል ሁኔታም በዓለም አቀፉ ኮሚቴ በኩል እንደማይኖር ያረጋግጣሉ።

አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ይህም ብቻ ሳይሆን ቻርተሩን የጣሱ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑንም አቶ ታምራት ይጠቁማሉ። ‹‹ተቋማት የሚመሩት በሕግና ደንብ ሆኖ ሳለ ይህንን መጣስ ትልቁ ጥፋት ነው፤ ለሌሎች ፌዴሬሽኖችም መልካም አርዓያ ሊሆን አይችልም። ስፖርቱን ለማሳደግ ሥርዓት ማበጀት አስፈላጊ ነው፤ ለሞራል መገዛትም እንደዚያው። ›› የሚሉት አቶ ታምራት፣ ስፖርቱ እየጎዱ የሚገኙ አካሄዶች በቀጣይ እንዳይባባሱ መንግሥት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ያወጣውን ደንብ የማስከበር ኃላፊነት እንዳለበት ያስረዳሉ። በመሆኑም እየተስተዋሉ የሚገኙ ችግሮችን በመመርመር መንግሥት ርምጃ መውሰድ እንደሚገባው አቶ ታምራት ምክረ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።